አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU

# የክወናና የዕይታ ጥበባት ትምህርት

## የተማሪ መማሪያ

## 4ኛ ክፍል



በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

# የክወናና የዕይታ ጥበባት ትምህርት

## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

# 4ኛ ክፍል

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

2014 ዓ.ም / 2021 /

# የክወናና የዕይታ ጥበባት ትምህርት

## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

**አዘጋጆች**

ኤልያስ ደምሴ

እንዳለ አባተ

በላይ አለማየሁ

ኢያሱ ስለሺ

ርብቃ ወንድማገኝ

የማታወርቅ ይታያል

**ገምጋሚዎች**

ኢየሩሳሌም በዳኔ

ማርቆስ ወልደሃና

ሰሎሞን ኃይለማርያም

**አስተባባሪ**

ጌታቸው ታለማ

**ሌይአውት ዲዛይን**

በእንጦጦ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ

© 2014ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን ጥቅሶችና ሥዕሎች በምንጭነት የተጠቀምንባቸውን ሁሉ እናመሰግናለን።

# ምስጋና

ይህን የትምህርት መጽኃፍ ከዝግጅት ጀምሮ በውጤት እንዲጠናቀቅ፣ የካበተ ልምዳቸውን በማካፈል፣በፓናል ውይይት ሃሳብ በማፍለቅና በማቅረብ፣ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ በማድረጋቸው ላደረጉት ከፍተኛ ድጋፍ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘላለም ሙላቱ የላቀ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

ለስራችን መሳካት ሁልጊዜ አብረውን በመሆን ፣ በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገም እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ ፣ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ ፣ የትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ ፣ የቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም መጽኃፉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ለስራው ልዩ ትኩረት በመስጠት አዘጋጅ መምህራንን ስለላካችሁልንና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችን እናቀርባለን፡፡

# ማውጫ

ርዕስ ገፅ

1. ምዕራፍ አንድ /ጥበባዊ ግንዛቤ/........................................................1
1.1 ማጤን ከሙዚቃ አንፃር ........................................................2
1.1.1 ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ የተሰሩ መዝሙራት ........................................2
1.1.2 ሙሉ ኖታና የእረፍት ምልክት ፡- ........................................2
1.1.3 የግማሽ ኖታና የእረፍት ምልክት፡- ........................................3
1.1.4 ሩብ ኖታ እና የእረፍት ምልክት፡-........................................4
1.2 ውዝዋዜ /ዳንስ/........................................................9
1.2.1 ድምፅ አልባ እንቅስቃሴን መረዳት ........................................11
1.3 ድራማ/ተውኔት........................................................12
1.3.1 ስለ የጠጣ ፍርድ ........................................................12
1.3.2 ስለ አንበሳና ስለ ነበር፣ ስለ ጅብና ስለ አህያ ባልንጀርነት......................14
1.3.3 ስለ አንድ ከበርቴ ሰው........................................................16
1.3.4 ድምፅ አልባ እንቅስቃሴ /ማይም/........................................18
1.3.5 እንቅስቃሴ........................................................18
ምን አየህ?........................................................19
1.4 የልዩ ልዩ ቅርጾች ፎርሞችና ቀለሞች ጥናት ........................................19
1.4.1 ፎርም ........................................................20
1.4.2 ነጻ "ልቅ" በተፈጥሮ ላይ የሚገኙ ኦርጋኒክ ቅርጾችን ........................21
1.4.3 ቀለሞች........................................................22
1.4.4 የቀለማት መገኛ ........................................................23
1.4.5 ቀለማትን ማወቅ ለምን ያስፈልጋል ........................................24
1.4.6 ቀለማትን ለመቀባት ምን ያስፈልግናል የቀለም ስነ ምግባሮች.................24
1.4.7 ዝርግና ቁም ፎቶግራፍ........................................................25
1.4.8 የፎቶ ግራፍ ጥቅሞች በጥቂቱ ........................................25
1.4.9 ዝርግና ቁም ፎቶግራፍ........................................................26
ማጠቃለያ፡- ........................................................27
አጠቃላይ ምዘና ........................................................28
2. ምዕራፍ ሁለት /ፈጠራን መግለፅ/........................................................29
2.1 የግልና/ቡድን ክዋኔ ከሙዚቃ አንፃር ........................................29
2.1.1 ስታፍ እና ክሌፎች........................................................30
2.1.2 ስታፍ........................................................31

2.1.3 ክሌፍ (የሙዚቃ ቁልፍ)......33
2.1.4 -ጂ- ክሌፍ (ትሬብል ክሌፍ) የቀጭን ድምፅ መፃፊያ......33
2.1.5 ኤፍ- ክሌፍ (ቤዝ ክሌፍ) የወፍራም ድምፅ መፃፊያ......35
2.1.6 ረዳት (ተጨማሪ መስመሮች) :- ......38
2.2 ባህላዊ ውዝዋዜ ......42
2.2.1 ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውዝዋዜ አይነቶች በጥቂቱ......43
2.3 የድምፅ አልባ ድራማና መነባነብ።......44
2.3.1 ድምፅ አልባ ተውኔት /ድራማ/ ......44
2.3.2 መነባነብ ......45
2.3.3 ግመል......45
2.4 ኮላዥን በአካባቢው ከሚገኝ ግብአት ተጠቅሞ ፎርሞችን፥ ለስላሳና ሸካራ ነገሮችን መስራት።......47
2.4.1 የቀጥታ ንድፍ፦ ......49
2.4.2 ሀሳባዊ ንድፍ፦......49
2.4.3 ፎርም እና ስራት (ልስላሴ እና ሸካራነት) ......52
2.4.4 ፎርም ......53
2.4.5 ልስላሴ እና ሻካራነት ......56
ማጠቃለያ ......58
ማጠቃለያ ምዘና፡-......58
3. ምዕራፍ ሦስት /ታሪካዊና ባህላዊ አውዶች/ ......61
3.1 ሙዚቃ በማኅበረሰብ ውስጥ ያለው ጠቀሜታ......62
3.1.1 የጦርነት ዘፈኖች፡- ......63
3.1.2 የለቅሶ ዜማዎች፡-......63
3.1.3 የሕፃናት ዘፈኖች ......63
3.1.4 ሙዚቃ በማህበረሰብ ውስጥ ከታሪክ አንፃር ያለው ሚና ......67
3.2 የውዝዋዜ ጥበብ በማህበረሰቡ ውስጥ ከባህልና ከታሪክ አንፃር ......68
3.3 የትያትር ጥበብ በማህበረሰቡ ውስጥ ከባህልና ከታሪክ አንፃር ያለው ሚና .70
3.3.1 ከእምነት አንፃር፡-......70
3.3.2 ከባህል አንፃር፡-......70
3.4.የዕይታ ጥበብ በማሕበረሰብ ውስጥ ከባህል እና ከታሪክ አንፃር ያለው ሚና 72
3.4.1 የዕይታ ጥበባት በማኅበረሰብ ውስጥ ከባህል አንፃር ያላቸው ሚና......73
3.4.2 የዕይታ ጥበባት በማኅበረሰብ ውስጥ ከታሪክ አንፃር ያላቸው ሚና......77
ማጠቃለያ ......80

ማጠቃለያ ምዘና:-......80
4. ምዕራፍ አራት /ሥነ-ውበታዊ እሴት (ዋጋ) ......82
4.1 ሙዚቃን መለማመድ ያለው ጠቀሜታ (ዋጋ)......84
4.1.1 ሀገር በቀል ሙዚቃዎችን ማወቅና ማድነቅ......86
4.1.2 የኢትዮጵያ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች......86
4.1.3 በትንፋሽ ድምፅ ከሚፈጥሩ መሳሪያዎች መካከል:-......87
4.1.4 በምት (ግጭት) ድምፅ የሚፈጥሩ መሳሪያዎች:-......87
4.1.5 የክር (በንዝረት) ድምፅ የሚፈጥሩ መሳሪያዎች......88
4.1.6 አራቱ የኢትዮጵያ ባህላዊ ቅኝቶች......90
4.1.7 የምንሰማባቸው መንገዶች......90
4.2 የውዝዋዜ ጥበብን መለማመድ ያለው ጠቀሜታ......92
4.3 የትያትር ጥበብን መለማመድ ያለው ጠቀሜታ......93
4.2.1 የማህበራዊ ኑሮን ልምድ ለመገንባት......94
4.2.2 አካልን ለማዳበር ይጠቅማል......94
4.2.3 አዕምሮን በእውቀት ለማዳበር......94
4.3 አገር በቀል ጨዋታዎች......95
4.3.1 ሞኝ ባልና ሚስት......95
4.4 የዕይታ ጥበብን መለማመድ ያለው ጠቀሜታ......96
4.4.1 ከስነ-ውበት አንፃር፦......97
4.4.2 ስሜትን ከመግለፅ አንፃር፦......97
4.4.3 ከስነ-አዕምሮ አንፃር፦......97
4.4.4 ከማህበረሰብ አንፃር፦......97
4.4.5 አገር በቀል የቤት አሰራሮችን፣ ጌጣጌጦችን ማወቅ እና ማድነቅ......98
ማጠቃለያ......100
የማጠቃለያ ምዘና......101
5. ምዕራፍ አምስት /ጥመርታ ዝምድናና፣ትግበራ/......102
5.1 ሙዚቃን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማዛመድ::......103
5.1.1 ሙዚቃን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማዛመድ::......104
5.2.1 ከዕፀዋትና ከእንስሳት እንቅስቃሴዎችና ውዝዋዜዎችን መቅዳት......108
5.2.2 ውዝዋዜ......108
5.4 የዕይታ ጥበብን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማዛመድ......111

5.4.1 ቅርፆችን፣ ፍርሞችንና ቀለማትን ከሒሳብ የትምህርት ዓይነትና ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማዛመድ ..... 112
5.4.2 የዕይታ ጥበብና የሒሳብ ትምህርት ጥምርታ ..... 112
5.4.3 የቅርፆች ዓይነት ..... 113
5.4.4 ሶስት ማዕዘን፦ ..... 113
5.4.5 ክብ፦ ..... 113
5.4.6 ካሬ፦ ..... 113
5.4.7 የዕይታ ጥበብና የሳይንስ ትምህርት ጥምርታ ..... 113
5.4.8 የቀለማት መዋሀድ ..... 114
ማጠቃለያ ..... 115
የማጠቃለያ ምዘና ..... 115
ዋቢ መፃህፍት ..... 117

# መግቢያ

የክወናና የዕይታ ጥበብ ለአንድ ሀገር ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነ-ልቦናዊ እድገት እጅግ አስፈላጊ ናቸው፡፡ በአለማችን በኢኮኖሚ አድገዋል ተብለው የሚታሰቡት ሃገራት በነዚህ የጥበብ ዘርፎች የላቀ ተጠቃሚነታቸውን አሳይተዋል፡፡ ባህላቸውንም ለሌሎች ሃገራት ለማስታዋወቅ እነዚህን ጥበባት በእጅጉ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡

በሃገራችን እነዚህ ጥበባት ሊያበረክቱት የሚችሉትን ዘርፈ ብዙ ጥቅም ለማግኘት በትምህርት የታገዘ ስልጠና መውሰድ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ የትምህርት ክፍል ተማሪዎች የተለያዩ ሀገር በቀል የክወናና የዕይታ ጥበባትን ትመለከታላችሁ፡፡ እነዚህ ጥበባትም ባህልን ከማስተዋወቅ፣ ታሪክን ከማስተላለፍ እና ትውልድን ከመቅረፅ አንፃር ያላቸውን ከፍተኛ ሚና ትረዳላችሁ፡፡

በዚህ ክፍል የተለያዩ የክወናና የዕይታ ጥበብ እወቀቶችን ትመለከታላችሁ ከነዚህም ውስጥ የቅርፅ ዓይነቶችን፣ ፍርሞችን ልዩ ልዩ ቀለማትን፣ የሙዚቃ ኖታዎችን ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ ከነእረፍት ኖታቸው፣ ድምፅ አልባ ድራማና መነባነብ ወዘተ ትረዳላችሁ፡፡ በተጨማሪም በመዘመርና በመወዛወዝ እንዲሁም የተለያዩ ስዕሎችን በመሳል የክወናና የዕይታ ጥበብ እውቀታችሁን ታዳብራላችሁ፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ጥበባዊ እውቀቶች ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር በማጣመርና በማዛመድ ለሌሎች ትምህርት አይነቶች የሚኖራችሁን ግንዛቤ እንድታዳብሩ ያግዛችኋል፡፡

## የትምህርቱ አጠቃላይ አላማ

- የቅርፅ ዓይነቶችን፣ ፎርሞችን ልዩ ልዩ ቀለማትን ትረዳላችሁ::
- የሙዚቃ ኖታዎች ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ ከነእረፍት ኖታቸው ትለያላችሁ::
- የድምፅ አልባ ድራማ ትሰራላችሁ::
- መዝሙራትን ትዘምራላችሁ::
- ውዝዋዜዎችን ትወዛወዛላችሁ::
- ቁምና ዝርግ ፍቶግራፎችን ታስረዳላችሁ::
- በድምፅና በምስል የሚያዩዋቸውንና የሚሰሟቸውን መልዕክቶችን ምስሎችንና ድርጊቶችን ታሳያላችሁ::
- የክሌፍ ዓይነቶችንና ክሌፍቹ የተቀመጡበትን ስታፍ መስመሮችና ባዶ ቦታዎች ከነረዳት መስመሮቻቸው ትለያላችሁ::
- በስታፍ ላይ (በስብስብ ላይ) የተፃፉትን (በመስመሮች ላይና በባዶ ቦታዎች ላይ የተፃፉትን) ሙዚቃዎች ትረዳላችሁ::
- ቤተሰባዊ ድርጊቶችን በመዝሙርና በውዝዋዜ ታከናውናላችሁ::
- በተሰጣቸው ትዕዛዝ (መመሪያ) መሰረት ሥዕሎችን ሥላችሁ፣ ኮላዥ ሰርታችሁ፣ የሚቀባውን ቀብታችሁ ታሳያላችሁ::
- የአገር በቀል ልምምዶች የሆኑትን የቤት አሰራሮችን፣ ማስዋቢያዎችን (ጌጣጌጦችን)፣ ሙዚቃዎችንና ጫወታዎችን ታደንቃላችሁ::
- በድምፅ አላባ ድራማና በመነባነብ መካከል ያሉትን ልዩነት ትለያላችሁ::
- በስዕልና በፍቶግራፍ መካከል ያሉትን ልዩነት ትለያላችሁ::
- ክ.እ.ጥ. ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለውን ጥመርታ ታስረዳላችሁ::
- የመዝሙራትን፣ የቅርፆችንና የቀለማትን አስፈላጊነት ታስረዳላችሁ:: ውዜዋዜዎችን ከዕፅዋትና ከእንስሳት እንቅስቃሴዎች ትኮርጃላችሁ::

# ምዕራፍ አንድ

## ጥበባዊ ግንዛቤ

### መግቢያ

በዚህ የትምህርት ደረጃና ዕድሜ ክልል ያሉ ተማሪዎች በክወናና ዕይታ ጥበባት ትምህርት በሙዚቃ፣ ውዝዋዜ፣ በትያትርና በዕይታ ጥበብ (በስነ-ስዕል) ትምህርት መስኮች ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ የተሰሩ መዝሙራት እና ውዝዋዜዎችን፤ ልዩ ልዩ ቅርፃ ቅርፆችን ፎርሞችንና ቀለሞችን ጥናት፤ ዝርግና ቁም ፎቶ ግራፍ በመጨረሻም ድምፅ አልባ እንቅስቃሴን በመረዳት ያላችሁን ዕውቀት እና ክህሎት እንድታዳብሩ ይጠበቃል፡፡

### አጠቃላይ አላማ፡-

- የቅርፅ ዓይነቶችን፣ ፎርሞችን ልዩ ልዩ ቀለማትን ታስረዳላችሁ፡፡
- የሙዚቃ ኖታዎች ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ ከነእረፍት ኖታቸው ትለያላችሁ፡፡
- የድምፅ አላባ ድራማ ትሰራላችሁ፡፡
- ቁምና ዝርግ ፍቶግራፎችን ታስረዳላችሁ፡፡

## 1.1 ማጤን ከሙዚቃ አንፃር

በዚህ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች በፅንሰ ሀሳብ ደረጃ እንዲሁም በተግባር ያገኙትን እውቀት ጠለቅ ባለ ሁኔታ እንድታሰላስሉ ያስፈልጋል።


**የትምህርቱ ዝርዝር አላማ፡-**

**ይህንን ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- ከሙሉ ኖታ እስከ እሩብ ኖታ ከነ እረፍት ምልክቶቻቸው በጊዜ ቆይታና በቅርጻቸው ትለያላችሁ።
- የሙዚቃ ኖታዎችንና የተቀመጡትን ሆሄያትን በአንድነት በማጣመር መዝሙሮችን ትዘምራላችሁ።
- ግጥሞችን በቃላችሁ ታጠናላችሁ።


### 1.1.1 ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ የተሰሩ መዝሙራት

1.1.2 ሙሉ ኖታና የእረፍት ምልክት ፡-ሙሉ ኖታና የእረፍት ምልክት ማለት ከሙዚቃ ኖታዎች መካከል ትልቁን የጊዜ ቆይታ የሚወክልና አራት ምት የጊዜ ቆይታ ያለው ነው። ከርዝመቱም አኳያ ትኩረት ተሰጥቶት መቆጠር ያለበትና ሙሉ ሃሳባችንን ቆጠራው ላይ እንዲሆን የሚፈልግ የኖታ አይነት ነው። የእረፍት ኖታውም እንደ ሙሉ ኖታ እኩል የጊዜ ቆይታ ያለው እና ልዩነታቸውም በቅርጻቸው እንዲሁም በእረፍት ኖታው ምልክቱ ምንም ድምጽ ሳይሰማ ጊዜውን ጠብቆ መጫወትን የሚያዝ ሙዚቃ መፃፊያ ኖታ ነው።



1፡- የሙሉ ኖታ ከነ አቻ የእረፍት ኖታ

1.1.3 የግማሽ ኖታና የእረፍት ምልክት፡- ማለት ከሙዚቃ ኖታዎች መካከል ከሙሉ ኖታ ቀጥሎ ትልቅ የጊዜ ቆይታን የሚወክል እና የሙሉ ኖታን ግማሽ ያክል የጊዜ ቆይታ አለው፡፡ ይህም ማለት ባለ ሁለት ምት የጊዜ ቆይታ ነው፡፡ የእረፍት ኖታው እንደ ግማሽ ኖታ እኩል የጊዜ ቆይታ ያለው እና ልዩነታቸውም በቅርጻቸው እንዲሁም በእረፍት ኖታው ምልክቱ ምንም ድምጽ ሳይሰማ ለሁለት ምት ያክል ጊዜውን ጠብቆ በዝምታ ማሳለፍ የሚያዝ የኖታ ምልክት ነው፡፡



ምስል 2፡- የግማሽ ኖታ የጊዜ ቆይታ ከነ አቻ የእረፍት ኖታ ምልክቱ

**1.1.4 ሩብ ኖታ እና የእረፍት ምልክት፡-** ከሙዚቃ ኖታዎች መካከል ባለ አንድ ምት የኖታ አይነት ሲሆን የግማሽ ኖታን ግማሽ የጊዜ ቆይታን የሚወክል ነው ፡፡ ከግማሽ ኖታ ጋር የሚለየው ክቡ የጠቆረ መሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም የእረፍት ኖታው እንደ ሩብ ኖታ እኩል የጊዜ ቆይታ ያለው እና ልዩነታቸውም በቅርጻቸው እንዲሁም በእረፍት ኖታው ምልክቱ ምንም ድምጽ ሳይሰማ ጊዜውን ጠብቆ መጫወት የሚያዝ ኖታ ነው፡፡





ምስል 3፡-የሩብ ኖታ የጊዜ ቆይታ ከነ አቻ የእረፍት ኖታ ምልክቱ

**መልመጃ 1፡-**

**የመዝሙር ርዕስ፡- ለበጎ ከሆነ (ድምፃዊ መሃሙድ አህመድ)**

ተከብረሽ
የኖርሽው
ባባቶቻችን ደም
ባባቶቻችን ደም፤
እናት ኢትዮጵያ
የደፈረሽ ይውደም
የደፈረሽ ይውደም፡፡

ተማሪዎች ይህን መዝሙር በምትዘምሩበት ጊዜ ሁለት ጥቅሞችን ታገኛላችሁ፡፡ የመጀምሪያው ተማሪዎች ከላይ በጽንሰ ሀሳብ ደረጃም ሆነ በተግባር ልምምድ ያወቃችሁትን የኖታ አነባበብ ዘዴ ከሆሄያት ጋር በማጣመር እንድትዘምሩ ሲያስችላችሁ በተጨማሪም መዝሙሩን በምትዘምሩበት ጊዜ ስለ ሀገር ፍቅርእና ሀገርን ስለመውደድ ትማሩበታላችሁ፡፡




## መልመጃ 2፡-


**የመዝሙር ርዕስ፡- ሠላም**

**ሠላም ሠላም ሠላም**

**ባለም ዙሪያ ሁሉ**

**ለሰው ዘር በሙሉ**

ተማሪዎች በዚህ መዝሙር ሰላም ለሰው ዘር በሙሉ በጣም አስፈላጊ እና ሰዎች በአብሮነት በደስታ ያለ ስጋት እንዲኖሩ የሚያስችል ሃብት መሆኑን ትረዳላችሁ፡፡ በተጨማሪም ይህንን መዝሙር ደጋግማችሁ በመዘመር የእያንዳንዱን ኖታዎች የጊዜ ቆይታን በአጥጋቢ ሁኔታ እንድትረዱ ያግዛችኋል፡፡




መልመጃ 3፡-

ይህ መዝሙር በተማሪዎች ተደጋግሞ የሚዘመር በመሆኑ ሆሄያትን እና ኖታዎችን በማጣመር በቀላሉ እንድትዘምሩ የሚያስችል መዝሙር ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ይህንን መዝሙር በምትዘምሩበት ጊዜ አንዱ ለአንዱ መረዳዳት ፣መተሳሰብን እንዲሁም መዋደድን ትገነዘባላችሁ፡፡

የመዝሙር ርእስ፡- ወንድሜ ያዕቆብ

ወንድሜ ያዕቆብ


ወንድሜ ያዕቆብ

ተኛህ ወይ ተኛህ ወይ

ደውል ተደወለ


ደውል ተደወለ

ተነሳ ተነሳ





**መልመጃ 1:-**

1. በሳጥኑ ውስጥ ከተቀመጡት ኖታዎች ምካከል የሙሉ ኖታን የእረፍት ምልክትን አክብቡ፡፡




2. በሳጥኑ ውስጥ ከተቀመጡት ኖታዎች መካከል የሩብ ኖታን የእረፍት ምልክትን አክብቡ፡፡



መልመጃ 2፡-

የሚከተለውን መዝሙር በማየት የጎደሉትን ሆሄያት ሙሉ፡፡

ተከብረሽ የኖርሽው
ባባቶቻችን ደም
ባባቶቻችን ደም፤
እናት ኢትዮጵያ
የደፈረሽ ይውደም
የደፈረሽ ይውደም፡፡




## 1.2 ውዝዋዜ /ዳንስ/

### የትምህርቱ ዝርዝር አላማ

ይህንን ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ስለ ባህላዊ ውዝዋዜ ትገነዘባላችሁ
- የተለያየ አይነት ኢትዮጵያዊ ባህላዊ ውዝዋዜዎችን ታውቃላችሁ

ውዝዋዜ ከስሜት የሚመነጭ የእንቅስቃሴ ጥበብ ማለት ነው። ዳንስ ወይም ውዝዋዜ በተለያየ የመልከአ ምድራዊ ክልል በተለያየ ባህል የሚገኝ ህዝቦች የሚያውቁት፣ የሚገለገሉበትና ለተለየ አላማቸው ሲሉ በወጉ የሚከሽኑት ጥበብ ነው።

ውዝዋዜ ከሰው ልጅ የፈጠራ ውጤቶች ማለትም የስነ-ጥበብ ዘርፎች የተለየ ባህርይ ያለው የጥበባት ዘርፍ ነው። ስሜት በአራት መሰረታዊ የአካል እንቅስቃሴዎች ይገለፃል። እነሱም በደስታ፣ ሀዘን፣ ፍራቻና ቁጣ ናቸው ።



ደስታ



ሀዘን



ቁጣ



ፍራቻ

በሀገራችን የተለያዩ አይነት ባህላዊ ውዝዋዜዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ ጉራጊኛ፣ ኦሮሞኛ፣ የአማራ እና ትግረኛ ለአብነት ይጠቀሳሉ፡፡

ተግባራዊ መልመጃ፡-

- ተማሪዎች የተለያዩ አይነት ብሔረሰብ ጭፈራዎችን እና ሙዚቃዎችን በመለማመድ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
- በግል እና በቡድን በመሆን በተለያዩ አይነት ባህላዊ ሙዚቃዎች በመወዛወዝ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

### 1.2.1 ድምፅ አልባ እንቅስቃሴን መረዳት

ከዚህ በፊት ትምህርታችሁ ስለ የድራማ አይነት እና አሰራር እንዲሁም ልዩ ልዩ ጨዋታዎች ተገንዝባችኃል፡፡ በዚህ በአራተኛ ክፍል የቀድሞ ግንዛቤያችሁን በማዳበር ስለ ድምፅ አልባ እንቅስቃሴ እና የተለያዩ ጨዋታዎች፤ ተረቶች በድራማዊ ይዘት እያላበሳችሁ እንድትጫወቱት እና ስለ ድራማ እና ድምፅ አልባ እንቅስቃሴ ልዩነት እድትረዱና ክህሎታችሁ እንዲዳብር ይጠበቃል፡፡

**የትምህርቱ ዝርዝር አላማ፡-**

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኃላ

- ስለ ድራማ ምንነትና አከዋወን ትረዳላችሁ፡፡
- ስለ ልዩ ልዩ የድራማ አይነቶች እየሰራችሁ ታሳያላችሁ፡፡
- ስለ ድምፅ አልባ እንቅስቃሴ ወይም ማይም ምንነት ትገነዘባላችሁ፡፡
- የድምፅ አልባ እንቅስቃሴ ትሰራላችሁ፡፡

## 1.3 ድራማ/ተውኔት

ተውኔት ወይም ድራማ ለተዝናኖት ፋይዳ ሲባል የሌሎችን ባሕርይ ሁናቴና ንግግር ለጊዜው ወርሶ ክዋኔን ከቋንቋ ጋር አገናኝቶ መጫወት ነው።

ድራማ ለእለት ተእለት ህይወት ትኩረት የሚሰጥ ጠንካራና በተመልካችም ዘንድ ተአማኒነትና ተቀባይነት ያለው በአነጋገር እና በተክለ ሰውነት በሚፈጠሩ እንቅስቃሴዎች የሚታገዝ ድርጊት ነው። ተውኔት ማለት "ተዋነየ ተጫወተ" ወይም ተጨዋወተ፣ ተነጋገረ እንደ ማለት ነው፡ በአጠቃላይ ጨዋታ፣ ዘፈን ድርጊትን እና እንቀስቃሴን ያካተተ ነገር ማለታችን ነው። ስለዚህ ተውኔት ስንል የእንግሊዘኛውን ድራማ የሚተካ ፍቺ አለው።

ተውኔት የሥነ ጽሁፋዊና አስመስሎ የማድረግ የመከወን ጥበቦች ቅንጅት

ነው። ሥነ ጽሁፋዊነቱ የሚመነጨው ከቃላት የተሰራ ከመሆኑ የተነሳ ሲሆን፣ አስመስሎ የማድረግ ጉዳዩ ደግሞ በገፀ ባህርያት ቦታ ገብተው (ተተክተው) በአካልና በግብር በመድረክ ላይ የሚከሰቱ ፍጡራንን ከማሳተፍ ላይ ነው። በጥቅሉ ሥነ ፅሁዊነትና ተተግባሪነት በተውኔት ውስጥ ቋንቋን እየተናገሩ ድርጊያዎችንም የሚፈፀሙ አካላት መኖራቸውን እንድናጤን ይረዳናል።

1. ከዚህ ከጥሎ የሚገኘውን የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴን ተረት አጥንታችሁ በድራማ መልክ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

### 1.3.1 ስለ የጦጣ ፍርድ

ሁለት ድመቶች ባንድነት ይኖሩ ነበር። አይጥ ለማደንም ቢሆን፤ ምናምንም ለመስረቅ ቢሆን አይለያዩም ነበር። አንድ ቀን ከአንዱ ቤት ወደ አንዱ ቤት ሽርሽር ሲሉ መስኮቱ የተከፈቱ ቤት አገኙ። በዚያ ጊዜ ድምጣቸውን አጥፍተው ቀስ እያሉ በመስኮቱ ዘለው ገቡ። በዚያም በእንቁላልና በሱኳር በሌላም በሚጣፍጥ ነገር የተሰናዳ ምግብ በጠረጴዛ ላይ አዩ። በጓዳውም አንድ ሰው እንኳ አለመኖሩን አይተዋልና ባንድነት ዘለው ያንን የጣፈጠ ምግብ አፋቸው እንደ ቻለላቸው ይዘው በመስኮት እየሾለኩ ወጡ። ከወጡም በኋላ በአታክልት ውስጥ ተደብቀው ለመብላት ሁለቱም የያዙትን ቀላቅለው አስቀምጠው ሰው እንዳያያቸው ግራና

ቀኝ ይመለከቱ ጀመር፡፡ ለመብልም በቀረቡ ጊዜ አንዱ ክፍል ምግብ ካንዱ በልጦ አዩት፡፡ በዚህም ምክንያት ትልቁ የኔ ነው፤ የኔ ነው በማለት ሁለቱ ድመቶች ተጣሉ፡፡ ምግቡን ትተው እርስ በርሳቸው ይሞጫጨሩ ጀመሩ፡፡

አንድ ጦጣም ባታክልት ውስጥ ሆኖ ይመለከታቸው ኑሮ፤ በቶሎ እየሮጠ መጥቶ እርስ በርሳችሁ ምን ያጣላችኋል? አሁን በአመጣችሁት ምግብ ተጣልታችሁ እንደ ሆነ፤ የአታክልቱ ውስጥ ዳኛ እኔ ነኝና ወደ ሸንጎ ቀርባችሁ በዳኛ ፊት ነገራችሁን መጨረስ ነው አላቸው፡፡

ድመቶቹም ይሁን ደግ ነው አሉ፡፡ እንግድያውስ ኑ አለና ወደ ዛፉ ሥር ሔዶ በጥላው ውስጥ አስቻለ፡፡ ከዚህም በኋላ ፍርዱን ጀመረ፡፡ ይህን ምግብ ሁለታችንም ባንድነት አይታችሁ አንስታችሁ የለምን አላቸው፡፡ አዎን፤ ስንገባም ባንድነት፤ ስናየውም ባንድነት፤ ስናነሣውም ባንድነት ነው አሉ፡፡ እንግዲያውስ ትክክል ተካፈሉ፤ ነገር ግን ትክክል ለመካፈል ሚዛን ያስፈልጋልና ሚዛን አምጥታችሁ ላካፍላችሁ አላቸው፡፡ ይሁን ብለው ሚዛን አመጡ፡፡

ቢመዝነው በውነትም አንዱ ክፍል ትልቅ ኑሮ ሚዛኑ ደፋ፡፡ ዳኛውም አንዱ መብለጡን አይቶ ልክ ላግባላችሁ ብሎ ከሚዛኑ ላይ አነሣና አንድ ጊዜ ገመጠለት፡፡ መልሶ ቢመዝነው ደግሞ ያ ትንሽ የነበረው በዛና ሚዛኑ

ደፋ፡፡ ደግሞ ያንን አንድ ጊዜ ገመጠና መልሶ ቢመዝነው የፊተኛው ሚዛኑ ደፋ፡፡ ሶስተኛ አንስቶ እገምጣለሁ ሲል ድመቶቹ ነገሩን አዩና ዳኛ ሆይ ተወው ተወው እኛው ተስማምተን እንካፈለዋለንና ስጠን አሉት፡፡

ዳኛው ጦጣም እነዲህ ሲል መለሰ፡ እመቤቶቼ ሆይ፤ እናንተ እንዲህ ብትሉ መቾ ይሆናል፤ ያጤ ስር አይደለምን፤ ሳላስተካክል ብሰጣችሁ ፍርድ መጉደሉ አይደለምን አለና ደግሞ አንድ ጊዜ ገመጠለት፡፡ እንደዚሁ ከዚያም ከዚያም እየገመጠ ጨረሰና፤ ጥቂት ሲቀረው ቢመዝነው ትክክል ሆነ፡፡ እነሆ አሁን ትክክል ሆነላችሁ አላቸው፡፡ እንግዲያውስ ስጠን አሉት፡፡

ጦጣ እነደገና መለሰ፡ ቆዩ አትቸኩሉ፤ እናንተ ነገሩ ሁሉ በመቸኮል የሚሆን ይመስላችኋል፡፡ እኔ ሥራዬን ሁሉ ትቼ እስካሁን ድረስ በናንተ ነገር ደክሜ ደክሜ እንዲያው ልቀር ነውን፤ ይህስ የዳኝነቴ ነው አለና ያንኑ የተረፈውን ወደ አፉ አድርጎ ከችሎት ተመለሰ፡፡ ድመቶቹም እያዘኑ ወደ ስፍራቸው ሔዱ፡፡

### የመልመጃ ጥያቄዎች

1. ከዚህ ታሪክ ምን ተማራችሁ ተመሪዎች?
2. ድመቶቹን ያጣላቸው ነገር ምንድን ነው?
3. ከ ጦጣ ፍርድ ምን ተማራችሁ?

ተማሪዎች ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴን ተረት የዱር አራዊቱን ሚና በመከፋፈል አጥንታችሁ ለመምህራችሁ በ ቡድን

አቅርቡ፡፡ የሚና አከፋፈሉም የአንበሳን፣ ጅብ፣ ነብር እና አህያ አንድ አንድ በመያዝ የሚናገሩት በማጥናት ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

### 1.3.2 ስለ አንበሳና ስለ ነብር፣ ስለ ጅብና ስለ አህያ ባልንጀርነት

አንበሳና ነብር፣ ጅብና አህያ ባልንጀርነት ይዘው ባንድነት ሊኖሩ ምግብ ተቸገሩ፡፡ አንድ ቀን ባንድነት ተሰብስበው ስለ ምግባቸው ምክር ጀመሩ፡፡ ከቶ እግዚአብሔር ምግብ የነሣን በምን ምክንያት ይሆን፤ ምናልባት ከመካከላችን ትልቅ ኃጢአት የሠራ እንዳለ ሁላችንም እንናዘዝ፤ ትልቅም ኃጢአት ሠርቶ የተገኘውን ከመካከላችን እናጥፋው ተባባሉ፡፡

መጀመሪያ አንበሳን ተናዘዝ አሉት፡፡ አንበሳም ሊናዘዝ ቀረበና፡ እኔ አንድ ቀን እጅግ ተርቤ ውዬ ነበርሁ፡፡ ዘላኖች ብዙ ከብት ይዘው በዱር ውስጥ በረት ሠርተው ተቀምጠው ነበርና ቀኑ ሲመሽ አይቼ በበረቱ ውጭ ቆሜ አንድ ጊዜ ባገሣ ሰንጋው ሁሉ በረቱን እየዘለለ ወጣ፡፡ እኔም አንዱን ሰንጋ ሰብሬ ደሙን ጠጥቼ ሥጋውን በላሁት፡፡ ይህ ኃጢአት እንደ ሆነ ፍረዱብኝ አለ፡፡

ባልንጀሮቹ መለሱ፤ ወዲህ ተርበህ ወዲህ ደግሞ በዱር ውስጥ የሚኖሩ ከብቶች አግኝተህ እንኳን አንድ ሰንጋ ብዙውንስ ብትበላ ምን ኃጢአት አለብህ ብለው ፈረዱለት፡፡

ነብር ቀረበ፤ እኔም አንድ ቀን እጅግ ተርቤ በዱር ውስጥ ወዲያና ወዲህ እያልሁ ምግብ ስፈልግ፤ አንዲት ፍየል ከእርኛዋ ጠፍታ ብቻዋን ቅጠላ ቅጠሉን ስትለቃቅም አገኘኋት፡፡ ወዲያው አንቄ ይዤ ደምዋን ጠጥቼ ሥጋዋን በላሁት፡፡ ይህ ኃጢአት እንደ ሆነ ፍረዱብኝ አለ፡፡

ባልንጀሮቹም መለሱ፡ ወዲህ ተርበህ ወዲህ ደግሞ ከእረኛዋ የጠፋች ፍየል አግኝተህ፤ እንኳን አንዲት ፍየል ብዙስ ብትበላ ምን ኃጢአት አለብህ አሉት፡፡

ጅብ ቀረበ፤ እኔም አንድ ቀን እጅግ ተርቤ ውዬ ነበረ፡፡ ማታ ከጉድጓዴ ወጥቼ ምግቤን ስፈልግ ነጋዶች ቢደክምባቸው ጥለውት የሔዱት አንድ የፈረሰ አጋሰስ፤ ከመንገድ ዳር ወድቆ መነሣት አቅቶት ሊገላበጥ አግኝቼ እርሱን በልቻለሁ፤ ይህ ኃጢአት እንደ ሆነ ፍረዱብኝ አለ፡፡

ባልንጀሮቹ መለሱ፡ ወዲህ ተርበህ ወዲህ ደግሞ ነጋዶች ጥለውት የሔዱ አጋሠሥ አገኘተህ፡ እንኳን አንድ አጋሠሥ ብዙስ ብትበላ ምን ኃጢአት አለብህ አሉት፡፡

ከዚህ በኋላ አህያን ነይ ተናዘዢ አሏት፡፡ አህያም ቀረበች፡፡ አንድ ቀን ጌታዬ ብዙ ጭነት ጭኖብኝ ስሔድ፤ ጌታዬ በመንገድ ላይ አንድ ሰው አገኘና ከዚያ እየተነጋገረ ቆመ፡፡ እኔም እጅግ ተርቤ ነበረና እነዚያ እስቲነጋገሩ ድረስ በመንገዱ ዳር ሠርዶ መሳይ አግኝቼ ያንን እየተነጫጨሁ ቆየሁ፤ ወዲያው ጌታዬ መጣና መጫኛውን አጠባብቆልኝ መንገዳችንን ተጓዝን፡፡ ይህ ኃጢአት እንደሆነ ፍረዱብኝ አለች፡፡

ባልንጀሮችዋም መለሱ፤ ከዚህ የበለጠ ምን ኃጢአት አለ፤ ጌታሽ ከሰው ጋር እስቲነጋገር ከመንገድ ወጥተሽ ሠርዶ እየነጨሽ የቆየሺው ትልቅ ኃጢአት አይደለምን፤ እግዚአብሔር ምግባችንን የነሣን ለካ ባንች ኃጢአት ኑረዋል፡፡

አንችን ከመካከላችን ካላጠፋን እግዚአብሔር አይታረቀንም ብለው ወዲያው ገነጣጥለው በሏት፡፡

ልጆቼ ሆይ፤ ከኃይለኞችና ከክፉ ሰዎች ጋር ባልንጀርነት አትግጠሙ፤ በክፋታቸው መክረው በኃይላቸው ያጠፉችኋልና።

መልመጃ 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ በፁሁፍ አብራሩ።

1. ተማሪዎች ከዚህ ታሪክ ምን ተማራችሁ?
2. አህያዋ የበሉዋት እነ አያአንበሶ ጥፋት አጥፍታ ነው ብላችሁ ታስባለችሁ? አዎ ካላችሁ ምንድ ነው ጥፋትዋ? አላጠፋችም ካላችሁም ምንድን ነው ምክንያቱ?
3. አያ አንበሶ ምንድን ነበር ያደረገው?

ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን አንድ ከበርቴ ሰው የተሰኘውን የብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ስላሴን ተረት በተገቢው መንገድ በማንበብ የሚና ክፍፍል በማድረግ አጥንታችሁ በቡድን በመለማመድ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

### 1.3.3 ስለ አንድ ከበርቴ ሰው

በእንግሊዝ ሀገር የሚኖር አንድ ከበርቴ ሰው ነበር። እርሱም ሦስት ልጆች ነበሩት። ነገር ግን ሰው ምንም ባለብዙ ገንዘብ ቢሆን ገንዘቡ ከሞት አያድነውምና ለሰውነቱ እንደ ሽመገለ የሞቱም ጊዜ እንደቀረበ አውቆ ሶስቱን ልጆቹን ጠርቶ ገንዘቡን ሁሉ አካፈላቸው። ርስቱንና ቤቱንም እንደሚገባቸው እያየ ሰጣቸው።

ነገር ግን አንድ ትልቅ አልማዝ ነበረውና ያንን ለብቻው በእጁ አንሥቶ ይዞ ልጆቼ ሆይ፤ ከእናንተ ከሦስታችሁ እጅግ ደስ የሚያሰኝ መልካም ሥራ ለሠራው ልጅ ይህን አልማዝ እሰጠዋለሁና የሰራችሁትን ሥራ ንገሩኝ አላቸው።

ታላቁ ልጁ ቀረበ። አባቴ ሆይ፡ አስቀድሞ የማያውቀኝ አንድ ሰው መጥቶ ብዙ ገንዘብ አደራ አስመቀጠብን። እርሱ መስጠቱን እኔ መቀበሌን አንድ ሰው እንኳን አላየም ነበር። እኔም አደራ አስቀምጫለሁ የሚል ወረቀት አልሰጡትም ነበር።

ከብዙ ቀን በኋላ ተመልሶ መጥቶ አደራ ያስቀመጥሁትን ገንዘብ ስጠኝ

አለኝ፡፡ በዚያ ጊዜም ከፍዬ አስቀርቼ የሰጠሽኝ ይኸ ብቻ ነው ብለው ወይም ጭራሽ አላየሁም ብለው ይቻለኝ ነበር፡፡ ዳሩ ግን ይህን ማድረግ አይገባም ብዬ አንድ እንኳ ሳላስቀር ገንዘቡን ሁሉ ሰጠሁት፡፡ ይህ መልካም ሥራ አይደለምን አለው፡፡

አባቱም መለሰ፣ ልጄ ሆይ፣ ይህ እውነተኛ ሰው ያሰኝሃል እንጂ ሥራ አይባልም አለው፡፡

መካከለኛው ልጁ ደግሞ ቀረበ፡፡ አባቴ ሆይ፤ አንዲት ሴት በባሕር ዳር ልጅዋን ታቅፋ ቆማ ጀልባ ወዲያና ወዲህ ሲመላለስ ስትመለከት ልጅዋ ከክንድዋ አምልጦ ወደ ባሕር ወደቀባት፡፡ እኔም የእርስዋን መጨነቅ አይቼ ለራሴ ሳላዝን ወደ ባሕሩ ውስጥ ገብቼ ልጅዋ ሳይሞት አወጣሁላት፡፡ ይህ መልካም ሥራ አይደለምን? አለው፡፡

አባቱ መለሰ፣ ልጄ ሆይ፣ ይህ ርኅሩህ ያሰኝሃል እንጂ ሥራ አይባልም አለው፡፡

ሦስተኛው ልጁ ቀበረ፡፡ አባቴ ሆይ፡ በደረቅ ውድቅት ብቻዬን ስሔድ ጠላቴ በገደል አፋፍ እንደተቀመጠ ወደያው እንቅልፍ ይዞት ሲያንጎላጅ አገኘሁት፡፡ በዚያ ጊዜ ጥቂት ብነካው በገደሉ ተንከባሎ ይወርድ ነበር፡፡ ወይም በታጠቅሁት ሰይፍ አንገቱን ብመታው ቆርጬ እጥለው ነበረ፡፡ ግን ይህንን ማድረግ አይገባም ብዬ ወደ እርሱ ቀርቤ እንዲነሣ ቀሰቀስሁት፡፡ የሚተኛበትም መልካም ሥፍራ አሳየሁት፡፡ ይህ መልካም ሥራ አይደለምን? አለው፡፡

አባቱም ይህን በሰማ ጊዜ የልጁን አንገት አቅፎ ይዞ ልጄ ሆይ፤ ልጄ ሆይ ከዚህ የሚበልጥ መልካም ሥራ የለምና ይህ አልማዝ የሚገባው ላንተ ነው ብሎ አልማዙን ሰጠው፡፡

### መልመጃ 3

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ በፁፍ  መልሱ

1. መልካም ስራ ምን ማለት ነው?
2. ርኅሩህነት በምን አይነት ስራ ይገለፃል?
3. እውነተኛነትስ አንደምን ያለ ነው?

### 1.3.4 ድምፅ አልባ እንቅስቃሴ /ማይም/

ማይም ማለት ፍቺው ውይም ትርጉዋሜው ድምጽ አልባ እንቅስቃሴ ማለት ነው፡፡ ማይም ራስን በእንቅስቃሴ ያለንግግር የመግለጽ ጥበብ ነው፡፡ የማይም ጥበብ የሚገለፀው በሰውነት ነው፡፡

### 1.3.5 እንቅስቃሴ

እንቅስቃሴ ማለት የአካላዊ ቦታ፣ የከፍታ የዝቅታ፣ የጥድፊያ ርጋታ እና የአቅጣጫ ለውጦች የእንቅስቃሴ አይነተኛ መገለጫዎች ናቸው፡፡

የመራመድ ዝቅ ማለት እና ከፍ የማለት የመሮጥ አንገት እና እጆችን በማንቀሳቀስ

ፊትን የተለያየ አይነት ቅርጽ ወይም ገፅታ እንዲኖረው ማድረግ፡ ፡

ከቦታ ቦታ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን እርምጃን፣ ሁለት እግሮችን በአንድ ላይ እያነሱ “መዝለል መሄድ፣ ሩጫ፣ በአንድ እግር እየዘለሉ መሄድን፡ የግልቢያ አይዕነት ሩጫ፡ መንሸራተት እና የተለያዩ እንቅስቃሴዎች አድርጉ፡፡  ከዚህ በመቀጠል የሚከተለውን ድምፅ አልባ እንቅስቃሴ ስሩ፡፡

ጨዋታ አንድ ፦ በዚህ ጨዋታ ልጆች የመረዳት አቅማቸውን የዳብሩበታል።

ምን አየህ?

ጨዋታ

በክፍል ውሰጥ ሆነ ከ ክፍል ውጭ በ ክብ ወይም በረድፍ በመቀመጥ ከፊት ለፊታቸው ቆሞ ያለውን መምህራችሁንም ሆነ የክፍል ጓደኛችሁን የፈለገውን ዐይነት ልዩ ልዩ ድርጊቶች በምልክት ወይም እንቅስቃሴ እየሰራ ያሳያችኃል። ምን እንደሰራ ያያችሁትን ነገር መናገር።

መልመጃ 4

የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ሃሰት በማለት መልሱ

1. ድምፅ አልባ እንቅስቃሴ የሰውነት አካላትን በመጠቀም የሚደረግ ክዋኔ ነው?
2. ንግግር በ ድምፅ አልባ እንቅስቃሴ ውስጥ ይፈቀዳል?
3. ድምፅ አልባ እንቅስቃሴ የሰውነት ቅልጥፍናን ይተይቃል?

የሚከተሉትን በ አጭሩ መልሱ

1. ድምፅ አልባ እንቅስቃሴ ምን ማለት ነው?
2. ድምፅ አልባ እንቅስቃሴ ተጠቅመን እንዴት መልዕክት ማስተላለፍ እንችላለን?

## 1.4 የልዩ ልዩ ቅርጾች ፎርሞችና ቀለሞች ጥናት

የትምህርቱ ዝርዝር አላማ

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሪዎች በኃላ፡-

- የልዩ ልዩ ቅርጾች ፎርሞችና ቀለሞችን ጥናት
- የቀለማትን አስፈላጊነት መገኛ ታውቃላችሁ
- የዝርግና የቁም ፎቶግራፍ ታውቃላችሁ

ቅርጾች ስንል የምናየው ነገር ዝርግና ጠፍጣፋ ምስል ሲሆን ዙሪያውን ልናየው የማንችለው ባለ ሁለት አውታረ መጠን ነው። በአይነታቸው የተለያዩ ናቸው። በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ነገሮች ሊገኙ ይችላሉ።

በተፈጥሮ የምናገኛቸው ቅርጾች "ነጻ" "ልቅ" እና ቅርጻቸው ለስያሜ የሚያስቸግሩ ናቸው "ምክንያቱም" በአይነት የተለያዩ ብዙ ናቸው።

ለምሳሌ ድንጋይ ደመና ቅጠላቅጠል የመሳሰሉት ለተፈጥሮ የምናገኛቸው "አርጋኒክ" እንላቸዋለን።

### 1.4.1 ፎርም


ፎርሞች ማለት ዙሪያቸውን ልንመለከታቸው የምንችላቸው አይነቶች ሲሆኑ ባለ ሶስት አውታር መጠን (3 ዳይሜንሽናል) እንላቸዋለን። በአካባቢያችን የት የት ይገኛሉ። ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፎርሞች በአካባቢያችን በሚገኙ ቁሳቁስ፣ተፈጥሮ፣ መጫወቻ ፣ወንበር፣ ጠረጴዛ ፣መጽሃፍ ላይ ሊገኙ ይችላል።





ምስል 1

የቅርጾች (ባለ ሁለት አውታረ መጠን)

ምስል 2








(ባለ ሶስት አውታር መጠን) (ፎርም)




ምስል 3

### 1.4.2 ነጻ "ልቅ" በተፈጥሮ ላይ የሚገኙ ኦርጋኒክ ቅርጾችን

**ተግባር 1፡ ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በእርሳስ ያላችሁ በዚያው ከለር ቀቡዋቸው**

1. በምሳሌው መሰረት ጠፍጣፋና ዝርግ የሆኑ የባለ ሁለት አውታር መጠን ቅርጾች ሳሉ

ምሳሌ:-



2. በምሳሌው መሰረት ዙሪያውን ልንመለከተው የምንችላቸው ባለ ሶስት አውታር መጠን ፎርሞችን

ምሳሌ:-




### 1.4.3 ቀለሞች

**የትምህርቱ ዝርዝር አላማ**

ተማሪዎች ይህን ርዕስ ከተማራችሁ በኃላ

- ስለ ቀለማት ታውቃላችሁ
- ቀለማት የት የት እንደሚገኙ ታውቃላችሁ
- ቀለማትን ማወቅ ለምን እንደሚያስፈልግ ታውቃላችሁ
- ቀለም ለመቀባት ምን እንደሚያስፈልግ ታውቃላችሁ

ቀለማት በአካባቢያች ፣በምንለብሰው ልብስ፣ በምንመገበው ምግብ እና ብርሀን ባለበት ቦታ ሁሉ ይገኛሉ። ቀለማትን ለማየት ብርሃን አስፈላጊ ነው። ቀለማት ከፍተኛ አድናቆትን ስሜትን የሚያሳድሩ ከመሆኑም በላይ በየእለቱ በምንኖራቸው ኑሮ ላይ ተፅእኖ ያደርጋሉ። የሰው ልጆች ቀለማት ልዩ ልዩ ትርጓሜ ይሰጣቸዋል።

የፍቅር፣ የሰላም፣ የተስፋ፣ የዘሀን እያለም ይጠቀምባቸዋል። በምንቀሳቀስበት ቦታ ሁሉ የምናያቸው ህንጻዎች፣ መኪናዎች፣ ልብሶች፣ የሰውን ልጅ የሚስቡ ተደርገው ይሠራሉ፣ ምክንያቱም የሰው ልጅ ከቀለማት ተለይቶ መኖር ስለማይችል ነው።

### 1.4.4 የቀለማት መገኛ

ቀለማት የማስታወስ ችሎታን ስለሚጨምሩልን ነገሮች "ይህ ቀለም አለው እያልን እንገልጻለን"

ለምሳሌ፡ ተፈጥሮ ፣ የባስ፣ የታክሲ፣ የተፈጥሮ እያልን እንገልጻቸዋለን


ምስል



### 1.4.5 ቀለማትን ማወቅ ለምን ያስፈልጋል

ቀለማትን ስናውቅ የምንስለውን ስዕል፣ የምንለብሰው ልብስ ለምንሄድበት ስፍራ ያሉ ምልክቶችን እንረዱለን በምክንያት እንጠቀምባቸዋለን

ምሳሌ




### 1.4.6 ቀለማትን ለመቀባት ምን ያስፈልግናል የቀለም ስነ ምግባሮች

- ቀለማትን ለመቀባት “መጀመሪያ” የምንስለውን ስዕል ሀሳብ ማወቅ ያስፈልጋል
- ቀለማትን ለመቀባት በምንስለው ስዕል ውስጥ ያለውን ሀሳብ ማወቅ ያስፈልጋል
- ሀሳባችንን ካወቅን በኃላ የስዕል ብሩሽ ፣ቀለም የልጆች የቀለም ወረቀት (ቻርት ፔፐር) የመሳሰሉትን እንጠቀማለን
- ስዕልን ስለን ስንጨርስ የተጠቀምንበትን ብሩሽ በጥንቃቄ ማጽዳትና አካባቢን ማጽዳት፣ ከዚያም እጅን መታጠብ በዕይታ ጥበብ ውስጥ አስፈላጊ ናቸው፡፡

መልመጃ 1፡- ተማሪዎች ቀለማትን ለመቀባት “የሚያስፈልጉን ስነ ምግባራት ምንድናቸው”?

### 1.4.7 ዝርግና ቋም ፎቶግራፍ

**የትምህርቱ ዝርዝር አላማ**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኃላ፡-

- ዝርግና ቋም ፎቶግራፍ ትማላራችሁ
- የፎቶግራፍ ጥቅሞችን ታውቃላችሁ
- ምስሎችን በመመልከት መልክቶችን ትለያላችሁ


የፎቶ ግራፍ ጥበብ አሁን እጅግ ረቂቅ ደረጃ የደረሰ ሲሆን በሀገራችን በአጼ ሚኒሊክ ዘመን ነው የተጀመረው

### 1.4.8 የፎቶ ግራፍ ጥቅሞች በጥቂቱ

- ታሪክን ለመመዝገብ
- መልካምድር ጥናትን ለማገዝ
- ተፈጥሮን በማጥናት (አዕዋፎችን እንስሳትን ዛፎችን…)
- ጊዜን ወደኃላ ያሳያናል

### 1.4.9 ዝርግና ቁም ፎቶግራፍ

ዝርግ ፎቶ ግራፍ አነሳስ በአብዛኛው ሰፊ ነገርን ለማንሳት የምንጠቀመው ሲሆን የቁም የፎቶግራፍ አነሳስ ግን ረዘም ያለ ነገር ለማንሳት የምንጠቀመው አይነት ነው፡፡




#### መልመጃ 2

1. ተማሪዎች ከዚህ በታች የተቀመጡትን ምስሎች በመመልከት ማንን እንደሚያመለክቱ ግለፁ

ምስል



--------------------------------------------

ተማሪዎች የፎቶግራፍ ጥቅሞች ዘርዝሩ

- -----------------------------
- -----------------------------
- -----------------------------
- -----------------------------

2. በትራፊክ በመብራት ህግጋት ውስጥ የቀለማቱን ትርጓሜ በጽሁፍ ግለጹ



----------------------------------------------------------

መልመጃ 3

- ባለ ሁለት አውታር መጠን ቅርጾች ሳሉ
- ባለ ሶስት አውታረ መጠን (ፎርም)
- ተፈጥሮ ላይ የምናገኛቸው ቅርጾች "ኦርጋኒክ" ሳሉ

ማጠቃለያ፡-

ስለ መሰረታዊ የኖታ ምልክቶች ማለትም ሙሉ ኖታ፣ ግማሽ ኖታ ሩብ ኖታ ከነ እረፍት ምልክታቸው ጠለቅ ባለ መለኩ አይታችኋል፡፡ በተጨማሪም ቀላል መዝሙራትን (ዜማዎችን) በሆሄያት ከኖታ ጋር እንድትለማመዱ ተደርጓል፡፡ እነዚህን ኖታዎች ተገቢውን ትኩረት ሰጥታችሁ በመደጋገም ተለማመዷቸሁ፡፡ ልዩ ልዩ ቅርጾችን ፎርሞችና ቀለሞችን አውቃችኋል፡፡ የዝርግና የቁም ፎቶ ልዩነትንም አውቃችኋል፡፡ በመሆኑም ልምምዳችሁን ባለማቋረጥ እውቀታችሁን እንድታዳብሩ ያስፈልጋል፡፡

## አጠቃላይ ምዘና

1. ተማሪዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ በመምረጥ መልሱ

1. አንድ ሙሉ ኖታ ከስንት ግማሽ ኖታ ጋር እኩል ይሆናል?

| | |
|---|---|
| ሀ. 4 | ሐ. 2 |
| ለ. 3 | መ. 4 |

2. አንድ ግማሽ ኖታ ስንት ሩብ ኖታ ይኖረዋል?

| | |
|---|---|
| ሀ. 1 | ሐ. 3 |
| ለ. 2 | መ. 4 |

3. ግማሽ ኖታ ስንት ምት አለው?

| | |
|---|---|
| ሀ. 1 | ሐ. 3 |
| ለ. 4 | መ. 2 |

4. የሩብ ኖታ የእረፍት ምልክት ስንት ምት አለው?

| | |
|---|---|
| ሀ. 1 | ሐ. 3 |
| ለ. 4 | መ. 2 |

5. ሩብ ኖታ ስንት ምት አለው?

| | |
|---|---|
| ሀ. 4 | ሐ. 2 |
| ለ. 3 | መ. 1 |

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ
1. ስዕልን ስለን ስንጨረስ ብሩሽን ማጠብ አስፈላጊ አይደለም፡፡
2. ስዕልን ለመሳል በሚያስፈልጉ ስነ ምግባሮች ውስጥ ሰርተው ሲጨርሱ እጇን መታጠብ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ፈጠራን መግለፅ

### መግቢያ

በክፍል አንድ ጥበባዊ ግንዛቤ ማጤን ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ የተሰሩ መዝሙራትና ውዝዋዜዎች፥ የልዩ ልዩ ቅርፃች፡ ፎርሞች እና ቀለሞች ጥናት የድምፅ አልባ እንቅስቃሴን መረዳት እና ስለዝርግና ቋም ፎቶገራፍ ተምራችኃል። በዚህ በክፍል ሁለት ፈጠራን የመግለፅ የግል እና የቡድን ክዋኔ ስለስታፍና ክሌፎች፡ ስለባህላዊ ውዝዋዜዎች፤ ኮላዥን በአካባቢው ከሚገኝ ግብአት ተጠቅሞ ፎርሞችን ልስላሴና ሸካራነት መስራት፥ መሰረታዊ ቀለማት እና ቀጥተኛ ህትመት እና የድምፅ አልባ ድራማ እና መነባነብ የምትማሩ ይሆናል።

**አጠቃላይ አላማ፡-**

- ስታፍ እና ክሌፎችን ትለያላችሁ።
- ባህላዊ ውዝዋዜዎችን ትለማመዳላችሁ።
- ኮላዥን በአካባቢው ከሚገኝ ግብአት ተጠቅሞ ፎርሞችን፥ ልስላሴና ሸካራነት ትለያላችሁ።
- መሰረታዊ ቀለማት እና ቀጥተኛ ህትመት ታውቃላችሁ።
- የድምፅ አልባ ድራማና መነባነብ ትለማመዳላችሁ።

### 2.1 የግልና/ቡድን ክዋኔ ከሙዚቃ አንፃር

ሙዚቃ ተማሪዎችን በቡድን በማቀናጀት ወደ ህብረት የማምጣት ትልቅ ኃይል አለው።

በመሆኑም ሙዚቃን በቡድን መስራት ትልቁ ጥቅም ተማሪዎች እርስበእርስ እንዲማማሩና አንዱ የሚያውቀውን ለሌላው በማሳወቅ ወደ ሚጠበቀው ውጤት በማምጣት አስተዋፅኦው ከፍተኛ ነው፡፡ በተጨማሪም ሙዚቃን በቡድን መስራት ተማሪዎችን ወደ አንድ ህብረት ለማምጣት ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡

የቡድን የሙዚቃ ብቃት የግልን የሙዚቃ ችሎታን ያዳብራል፡፡ ተማሪዎች የግል የሙዚቃ ብቃታቸው ማደግ ለሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ውጤታማ ለመሆን ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡


### 2.1.1 ስታፍ እና ክሌፎች

**ዝርዝር የመማር ውጤት**

- የክሌፍ ዓይነቶችንና ክሌፎቹ የተቀመጡበትን ስታፍ መስመሮችና ባዶ ቦታዎች ከነረዳት መስመሮቻቸው ትለያላችሁ፡
- በስታፍ ላይ (በስብስብ ላይ) የተፃፉትን (በመስመሮች ላይና በባዶ ቦታዎች ላይ የተፃፉትን) ሙዚቃዎች ትረዳላችሁ፡፡

### 2.1.2 ስታፍ

ስታፍ ማለት የሙዚቃ መፃፊያ ሠሌዳ ነው። ስታፍ የሚሰራው በአምስት ትይዩ መስመሮች እና በአምስቱ መስመሮች መካከል በሚገኙት አራት ክፍት ቦታዎች ነው። የነዚህ አምስት መስመሮችና አራት ክፍት ቦታዎች ጥቅም እያንዳንዱን የሙዚቃ ድምፆች ባላቸው ቃና (የድምፆች መቅጠንና መወፈር) መሰረት አንድ ጊዜ መስመር ላይ ቀጥሎ ክፍት ቦታ ላይ በማሰቀመጥ ኖታወችን ወደላይም ወደታችም መፃፍ ማስቻል ነው። በዚህም ምክንያት ስታፍን መረዳት ሙዚቃን የመፃፍ እና የማንበብ ዘዴን ማወቅ ነው።




ምስል 1፡- ስታፍ መስመር

ስታፍን በቀላሉ በወረቀት ላይ ለመሳል ከታች ወደ ላይ ወይም ከላይ ወደታች አምስት መስመሮችን እናሰምራለን እነዚህ መስምሮች በራሳቸው አራት ክፍት ቦታዎችን ይፈጥሩልናል።

የመስመርና የክፍት ቦታዎቹ ስያሜ በእንግሊዝኛ ፊደል ወይም በላቲን ስያሜ አማካኝነት ነው።


ኖታ ስታፍ (መፃፊያ ሰሌዳ) ላይ የምንቆጥረው (የምንፅፈው) መስመርና ክፍት በታዎችን ተራ በተራ እያፈራረቅን ከታች ወደላይ ነው፡፡




ምስል 2፡- የስታፍን መስመሮችና ክፍት በታዎች ስንቆጥር ከታ ወደላይእንደሆነ የሚያሳይ ምስል ፡፡

ከትንሿ ጣት አንድ ብለን ጀምረን ወደ አራተኛ ጣት ከዛም ሶስተኛ ጣት

መቁጠር




ምስል 3፡- በእጅ ተጠቅሞ ስታፍ መገንዘብ

በስታፍ ላይ የሙዚቃ ድመፆችን ማስቀመጥ የድምፆች መቅጠንና መወፈርን ይወክላሉ፡፡ እነዚህም ድምፆች ሁለት የተለያየ መጠሪያ ስሞች መጠቀም እንችላለን፡፡

እነርሱም:-

| በቁጥር | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የላቲን ስም | Do | Re | Mi | Fa | Sol | La | Si(Ti) |
| የእንግሊዝኛ ስም | C | D | E | F | G | A | B |

የሙዚቃ ድምፆችን በስታፍ መስመሮችና ክፍት ቦታዎች ላይ ያላቸውን ቦታ ለማወቅ የሚረዳን ምልክት ክሌፍ (የሙዚቃ ቁልፍ) በመባል ይታወቃል፡፡

መልመጃ 1፡-

1. በወረቀት ላይ ስታፍ መስመር አስምሩ
2. ሰባቱን የሚዚቃ ድምፆች ስያሜዎቹን በላቲንና በእንግሊዘኛ ፃፉ

### 2.1.3 ክሌፍ (የሙዚቃ ቁልፍ)


ሁልጊዜ በስታፍ በስተግራ መጀመሪያ ላይ የሚቀመጥ ሲሆን የሙዚቃ ድምፆችን በስታፍ መስመሮችና ክፍት ቦታዎች ላይ ቦታቸውን የሚወስንል የሙዚቃ ቁልፍ ነው፡፡ በሙዚቃ ውስጥ የተለያዩ አይነት ክሌፎች ሲኖሩ እነርሱም G ክሌፍ ወይም ትሬብል ክሌፍ (የቀጭን ድምፅ መፃፊያና)፣ F ክሌፍ ወይም ቤዝ ክሌፍ (የወፍራም ድምፅ መፃፊያ) ዋነኞቹ ናቸው፡፡
በዚህ የክፍል ደረጃ የምንዳስሳቸው ትሬብል ክሌፍንና ቤዝ ክሌፍን ይሆናል፡፡

**2.1.4 -ጂ- ክሌፍ (ትሬብል ክሌፍ) የቀጭን ድምፅ መፃፊያ** ፡- በአንፃራዊነት ቀጫጭን ድምጾችን የምንፅፍበት ሲሆን በዚህ የክሌፍ ዓይነት -G- ድምፅን ከሁለተኛው መስመር ላይ በመጀመር ፊደሎቹን በቅደም መስመር ክፍት ተከተል መስመር ክፍት ቦታ እያልን ተራ በተራ የምንፅፍበት ምልክት ነው፡፡

የሙዚቃ ድምፆች አፃፃፍ ከታች ወደላይ ወይም ከላይ ወደ ታች በቅደም ተከተል ይሆናል፡፡




ምስል 4፡- -ጂ- (G) ክሌፍ ምልክት




ምስል 5፡- -ጂ- (G) ክሌፍ ቁልፍ በስታፍ ላይ የአፃፃፍ ቅደም ተከተል


የ -ጂ- ክሌፍን በስታፍ ውስጥ የሚገኙትን የሙዚቃ ድምፆች ለማስቀመጥ የምንጠቀምብት ዘዴ በመጀመሪያ -ጂ- (G) ድምፅን ሁለተኛ መስመር ላይ ካገኘን በኂላ የሚቀጥለውን ድምፅ ከሁለተኛ መስመር በላይ ባለው (ሁለትኛ ክፍት ቦታ ላይ) -ኤ- (A) ድምፅን እናስቀምጣለን ፡፡ የተቀሩትን ድምፆች መስመር ክፍት ቦታ መስመር ክፍት ቦታ በማድረግ በቅደም ተከተል እንደረድራለን ፡፡በተጨማሪምከ ጂ ሁለተኛው መስመር በታች ባሉት ክፍት ቦታ እና መስመር አንደኛ ክፍትቦታ ላይ -ኤፍ- (F) በማሰቀመጥ ቀጥሎ በምናገኘው አንደኛ መስመር ላይ -ኢ-(E) እናሰቀምጣለን፡፡




ምስል 6፡- የጂ ክሌፍ መስመሮች እና ክፍት ቦታዎች ላይ
ያሉ ድምፆች በስታፍ ላይ አቀማመጥ

የ -ጂ- G ክፍል አምስቱ መስምሮች ላይ የሚቀመጡ ድምፆች E-G-B-D-F ሲሆኑ በተቀሩት አራት ክፍት ቦታዎች ላይ የሚቀመጡ ድምፆች ደግሞ

F-A-C- E ናቸው።




ምስል፡- 6 መስመርና የክፍት ቦታዎች ስያሜ


መልመጃ 2፡-

1. የ-ጂ- ክሌፍ መነሻው ስንተኛው መስመር ነው
2. የ-ጂ- ክሌፍ የክፍት ቦታ ድምፆች ፃፉ።
3. የ-ጂ- ክሌፍ መስመር ላይ ድምፆች ፃፉ።
4. -ጂ- ክሌፍን በወረቀት ላይ ስታፍ ሰርታችሁ ስላችሁ አሳዩ።

2.1.5 ኤፍ- ክሌፍ (ቤዝ ክሌፍ) የወፍራም ድምፅ መፃፊያ፡- ይህ የክሌፍ ዓይነት ወፋፍራም ድምፆችን ለመፃፍ የሚረዳን ሲሆን በዚህ የክሌፍ ዓይነት -ኤፍ- F ድምፅን በአራተኛው መስመር ላይ የምናገኘው ይሆናል። የተቀሩትን የሙዚቃ ድምፆችን ደግሞ ኤፍ ድምፅን መነሻ በማድረግ ወደ ላይ እና ወደ ታች በስታፍ መስመርና ክፍት ቦታዎች ላይ በቅደም ተከተል የቀሩትን የሙዚቃ ድምፆችን ማስቀመጥ ይቻላል።




ምስል 7፡- የቤዝ ክሌፍ (ኤፍ ክሌፍ) ምልክት





ምስል 7፡- ኤፍ ድምፅ በስታፍ አራተኛ መስመር ላይ ሲቀመጥ

የ -ኤፍ- F ክሌፍን በስታፍ ውስጥ የሚገኙትን የሙዚቃ ድምፆች ለማስቀመጥ የምንጠቀምብት ዘዴ በመጀመሪያ የኤፍ Fን ድምፅ አራተኛ መስመር ላይ ካገኘን በኋላ የሚቀጥለውን ድምፅ ከአራተኛ መስመር በላይ ባለው (አራትኛ ክፍት ቦታ ላይ) ጂ (G) እና አምስተኛ መስመር ላይ ኤ (A) ድምፅን እናስቀምጣለን ፡፡ የተቀሩትን ድምፆች ከኤፍ መስመር ወደ ታች ክፍት ቦታ  መስመር ክፍት ቦታ መስመር ላይ በማድረግ በቅደም ተከተል እንደረድራለን ፡፡




ምስል 8፡- የ ኤፍ ክሌፍ መስመሮች እና ክፍት ቦታዎች ላይ ያሉ ድምፆች በስታፍ ላይ አቀማመጥ

ከላይ እንደተገለፀው ስታፍ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት፡፡ እነርሱም አምስቱ መስመሮች ላይ የሚቀመጡ ድምፆች እና አራቱ ክፍት ቦታዎች ላይ የሚቀመጡ ድምፆች ናቸው፡፡ የ ኤፍ ክሌፍ አምስቱ መስምሮች ላይ የሚቀመጡ ድምፆች G- B-D-F-A ሲሆኑ በተቀሩት አራት ክፍት ቦታዎች ላይ የሚቀመጡ ድምፆች ደግሞ A-C-E-G ናቸው፡፡ይህንን ማንበብ የምንጀምረው ከታችኛው መስመር ወደላይ ነው፡፡





ምስል9፡- የ ኤፍ ክሌፍ በመስመር እና ክፍት ቦታዎች ላይ ያሉ ድምፆች በስታፍ ላይ አቀማመጥ፡፡

መልመጃ 3፡-


1. የ-ኤፍ- ክሌፍ መነሻው ስንተኛው መስመር ነው
2. የ-ኤፍ- ክሌፍ የክፍት ቦታ ድምፆች ፃፉ፡፡
3. የ-ኤፍ- ክሌፍ መስመር ላይ ድምፆች ፃፉ፡፡
4. -ኤፍ- ክሌፍን በወረቀት ላይ ስታፍ ሰርታችሁ ስላችሁ አሳዩ፡፡

2.1.6 ረዳት (ተጨማሪ መስመሮች) ፦ እነዚህ መስመሮች አጫጭር እና ወደ ጎን የተሰመሩ መስመሮች ሲሆኑ ከስታፍ ውጪ በላይና በታችኛው ክፍል የሚጨመሩ ናቸው፡፡ ሙዚቃ ድምፆች በስታፍ ውስጥ ባሉ መስመርና ክፍት ቦታዎች የሚገደብ ባለመሆኑ ድምፆች ከስታፍ (ከአምስቱ መስመሮች) ውጪ እየቀጠኑ እና እየወፈሩ ሲሄዱ እነዚህን ድምፆች ለመፃፍ የምንጠቀምባቸው መስመሮች ናቸው፡፡ እነዚህን ረዳት መስመሮች የምንፅፍበት መንገድ ልክ ስታፍ ላይ እንደተጠቀምነው መስመር - ክፍት ቦታ መስመር - ክፍት ቦታ በማድረግ በቅደም ተከተል እናስቀምጣቸዋለን፡፡


እነዚህ አጫጭር አግድም መስመሮች ሁሉም ነገራቸው (ስማቸውም፣ አገልግሎታቸው፣ በእያንዳንዳቸው አጭር መስመሮች መካከል የሚኖረው ክፍተት ጭምር) ልክ እንደ ስታፍ ነው፡፡




ምስል 10፦ የላይኛው ረዳት መስመሮች




ምስል 11፦ የታችኛው ረዳት መስመሮች



ምስል12:- የታችኛውና የላይኛው ረዳት መስመር ድምፆች አቀማመጥ




ምስል 13:- የ -ጂ- ክሌፍ ስታፍ ውስጥ ያሉ ድምፆች እና ረዳት መስመር።




ምስል 14:- የ -ኤፍ- ክሌፍ ስታፍ ውስጥ ያሉ ድምፆች

- ከዚህ በፊት የምናውቃቸው ኖታ ምልክቶችን (ሙሉ ኖታ፣ ግማሽ ኖታ፣ ሩብ ኖታ ከነአቻ እረፍት ኖታ) በስታፍ ላይ በመስመር ወይም በክፍት ቦታ ላይ ማስቀመጥ እንችላለን፡፡
- ኖታዎችን ክሌፍ ባለው እስታፍ ላይ ስንፅፍ ከምት በተጨማሪ ድምፅ ይኖራቸዋል፡፡


መልመጃ 4፡- ቀጥሎ ያሉትን ኖታዎች በተፃፈው መሰረት ዘምሩ፡፡



መልመጃ 5፡- ቀጥሎ ያለውን ትዊንክል ወይም ኤቢሲዲ ዜማ መዝሙርን በኖታው መሰረት ዘምሩ፡፡



መልመጃ 3፡- ቀጥሎ ያለውን የኖታ ድርደራ ለየብቻ ተለማምዳችሁ ዘምሩ፡፡




መልመጃ 6፡- የሚከተሉትን ጥቄዎች እውነት ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

1. ከስታፍ ውጪ ከላይና ከታች ሙዚቃን ለመፃፍ የሚገለግሉ መስመሮች ረዳት መስመሮች ይባላሉ፡፡ ______________
2. ከስታፍ ውጪ በረዳት መስመሮች የሙዚቃ ድምፆችን ለመደርደር መስመር-ክፍት ቦታ ፣ ክፍት ቦታ መስመር የሚለውን ቅደም ተከተል መጠበቅ የለብንም፡፡ ______________
3. የሙዚቃ ኖታዎች በስታፍ ላይ ሲፃፉ የጊዜ ቆይታ ብቻ ይወክላሉ፡፡ ______________
4. የክሌፍ ምልክቶች ከእስታፍ ከፊት ለፊት ሚፃፉ ናቸው፡፡ ______________
5. የላቲን ስያሜዎች ኤ-ቢ-ሲ-ዲ-ኢ-ኤፍ-ጂ ናቸው፡፡ ___________

## 2.2 ባህላዊ ውዝዋዜ

ባህል ሰፊ እና ውስብስብ ነገር ሲሆን፥ ዕውቀትን፥ ዕምነትን፥ ጥበብን፥ ህግን፥ ፀባይን እና ልምድን ያካትታል።እነዚህና ሌሎች ልምዶችን የማህበረሰቡ አባል በመሆን የሰው ልጅ የሚለምዳቸው ናቸው።

ባህላዊ ውዝዋዜ የማህበረሰቡን መልከአምድራዊ አኗኗር፥ ልማድ እና እሳቤ ምልከታ በሰውነት እንቅስቃሴ በመደገፍ የሚደረግ ነው። በሀገራችን ኢትዮጵያ ከ ሰማንያ በላይ ብሔረ-ሰብ ያለባት ትልቅ እና ቀደምት ሀገር ናት። እያንዳዱ ብሔረ-ሰብ የራሱ የሆነ የባህላዊ ውዝዋዜ ወይም ዳንስ ስልት አለው። እነዚህ ልዩ ልዩ የሆኑ የባህላዊ ውዝዋዜ ስልቶች በይበልጥ የሚያተኩሩበትን የሰውነት አካል ክፍል እንቅስቃሴ ብንመለከት፦

- ለምሰሌ፦ - ትግርኛ፦ ባህላዊ ውዝዋዜ ከሌላው ሰውነት አካል ክፍል በአመዛኙ በእግር በመጠቀም ይታወቃል ከዛ ባለፈ አንገት እና እጅ በመጠቀም የሚታወቅ የሰሜኑ አገራችን ክፍል ነው።
- ጉራጊኛ፦ ከሌላው የሰውነት ክፍል በበለጠ እጅ እና እግርን በማጣመር የሚደረግ የ ባህላዊ ውዝዋዜ እንቅስቃሴ አይነት ነው።
- ኦሮምኛ፦ በአመዛኙ በአንገት እና በእግር ጥመረት የሚደረግ የባህላዊ ውዝዋዜ እንቅስቃሴ አይነት ነው።
- ደቡብ፦ በአመዛኙ በዳሌ እና በእግር ጥምረት የሚደረግ የባህላዊ ውዝዋዜ አይነት ነው።
- አማርኛ፦ በአመዛኙ የትከሻ እንቅስቃሴን እስክስታ በመባል የሚታወቅ የባህላዊ ውዝዋዜ አይነት ነው።

ከብዙ በጥቂቱ የሀገራችንን የባህላዊ ውዝዋዜ አይነቶች እና የሚያተኩሩባቸውን የሰውነት ክፍሎች ለመዳሰስ ተሞክሩዋል። በዚህም እያንዳንዱ ውዝዋዜ የሚገለፅበት መንገድ በራሱ ልዩነት እና አንድነት አለው ይህንንም ከላይ መመልከት ይቻላል።

ቀጥሎ የቀረቡትን የውዝዋዜ አይነቶች ተመልከቱ፦

### 2.2.1 ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውዝዋዜ አይነቶች በጥቂቱ

ወላይትኛ







አማርኛ

ትግርኛ





ኦሮምኛ

ጉራጊኛ

### መልመጃ 1

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በማብራራት መልሱ።

1. ባህል ምን ማለት ነው?
2. የኦሮምኛ እና የጉራጊኛ ባህላዊ ውዝዋዜ የሚያተኩሩበት የሰውነት ክፍልን ግለፁ?
3. የአማርኛ፥ ደቡብ እና ትግሪኛ ጭፈራዎችን የእንቅስቃሴ መገለጫ አብራሩ?

## 2.3 የድምፅ አልባ ድራማና መነባነብ።

**የትምህርቱ ዝርዝር አላማዎች**

- ድምፅ አልባ ድራማ ትሰራላችሁ።
- የድምፅ አልባ ድራማ ምንነት ትረዳላችሁ።
- ስለ መነባነብ ምንነት ትረዳላችሁ።
- መነባነብታቀርባላችሁ።

### 2.3.1 ድምፅ አልባ ተውኔት /ድራማ/

በክፍል አንድ ትምህርታችን ድምፅ አልባ እንቅስቃሴ ወይም ማይም ራስን በእንቅስቃሴ ያለ ንግግር የመግለጽ ጥበብ ነው። የማይም ጥበብ የሚገለፀው በሰውነት ነው ብለናል። በዚህ በክፍል ሁለት ስለ ድምፅ አልባ ድራማ ምንነት እና ክዋኔ የምትማሩ ይሆናል።

ድምፅ አልባ ተውኔት ማለት ቃለ-ተውኔት ሳይኖርበት በመድረክ እንቅስቃሴ መግለጫ ብቻ ተፅፎ የሚተወን ተውኔት ነው። በሌላ አባባል ድምፅ አልባ ተውኔት ማለት በሰውነት የአካል ክፍሎች እንቅስቃሴ አማካኝነት የሚቀርብ የሰውነት ንግግር ነው። በዚህ ድምፅ አልባ ድራማ እውቅናን ካተረፉ ሰዎች መካከል እንግሊዛዊው ቻርሊ ቻፕሊን በዋነኝነት ተጠቃሽ ነው። ተማሪዎች የቀን ውሎዋችሁን በድምፅ አልባ እንቅስቃሴ በመስራት በጓደኞቻችሁ ፊት በመውጣት ለመምህራችሁ እንዲሁም በቤታችሁ አሳዩ። ለምሳሌ፡ ጠዋት ከዕንቅልፍ ስትነሱ፥ ፊታችሁን ስትታጠቡ፥ ቁርስ ስትበሉ፥ እንዲሁም ትምህርት ቤት ስትሄዱ ወ.ዘ.ተ-- ያደረጋችሁትን በድምፅ አልባ እንቅስቃሴ ግለፁ።

## 2.3.2 መነባነብ

በአንድ ተዋናይ ብቻ መድረክ ላይ የሚደረግ ግለ ንግግር ነው። ተዋናዩ የሚያሰማው መነባነብ በአብዛኛው ውጫዊውን ግጭት የሚመለከት እንጂ እንደ ንባበ አዕምሮ ውስጣዊውን ግጭት አያሳይም።

ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን ታሪክ በማንበብ ስለ ግመል የተረዳችሁትን ለመምህራችሁ አቅርቡ።

## 2.3.3 ግመል

ግመል ከፈረስ ይበልጣል፤ በአካሉም ከሌሎች እንስሳት የተለየ ረዢም ነው፡ ፡ ሲጫንና ሲራገፍ፤ ሰው ሲወጣበትም ሳለ ሲወርድም ይንበረከካል። ሲቆምም ባሰበ ጊዜ መጀመሪያ የኋላ እግሮቹን ያነሳል። ሰው ተቀምጦበትም ሲነሳ አጥብቆ ያልያዙ እንደ ሆነ ሰውዩው ወደ ግመሉ ራስ ይወረውራል ግመል ብርቱ ነው፤ ከባድ ዕቃም ለመሸከም ይችላል።

በሰሜን ሕንድ በዐረብ አገርም፤ በአፍሪቃ በረሃዎችም በጣም ይጠቅማል። ውሃ ሳይጠጣም ብዙ ርቆ ይሄዳል ውሃም በሌለበት አሸዋ በሆነ ስፍራ ካንድ ቦታ ወደ ሌላው ለመዝለቅ የተደራጀ ነው። አራት አምስት ቀንም ያህል ውሃ ሳይጠጣ ለመሄድ ይችላል።

አንዳንድ ግመሎች በጀርባቸው አንድ እኩሌቶቹም ሁለት ሻኛ አላቸው፡፡ ሻኛቸውም የሰባ ነው፡፡ ግመሉ ሳይበላ አያሌ ቀን በተቀመጠ ጊዜ ሻኛው እየሚሸሽ ይሄዳል ባይበላም እንኳ ሻኛው ጉልበት ይሆነዋል፡፡

የግመሉ እግሮች ትልልቅ ሰፊና ለስላሳ በወፍራም ቆዳ የተያያዙ ናቸው፡፡ በበረሃ ውስጥ ባለ በሞቀ አሸዋ ላይ በቀላል አካሄድ መራመድ ይችላሉ፡፡ ግመል ሲሄድ በጸጥታ ነውና፡፡ ባጠገብህ ሲያልፍ አትሰማውም፡፡

የግመሉ አፍንጫ ጠባብ ሥንጣቂ ያለው መዘጋት መከፈት የሚችል ነው፡፡ አሸዋው በነፋስ በተበተነ ጊዜ ግመሉ ይተኛና አፍንጫውን ዘግቶ ራሱን በአሸዋ ይቀብረዋል፡፡ ከሩቅም የውሃ ሽታ ይሰባል፡፡

አንዳንድ ጊዜ መንገድ አሳብሮ በቀጥታ ይሄድና ወደ ውሃ ይደርሳል፡፡ በዚህ አኳኋን ብዙዎችን መንገደኞች ውሃ ካለበት ያደርሳቸውና ከውሃ ጥም ያድናቸዋል፡፡

ነጋዴዎች በግመል ዕቃቸውን ይጭናሉ፤ ግመሎችም ጅምላ ሁነው ይጓዣሉ፡፡ ጉዞውም እስከ ሰባና እስከ መቶ ይደርሳል፡፡

አንዳንድ ጊዜም በተርታ ተቀጣጥለው ይሄዳሉ፤ አንዳንዶችም ግመሎች ጠንካሮች ናቸው፡፡ ባንድ ቀን ከመቶ ኪሎ ሜትር የሚበልጥ መንገድ መሄድ ይችላል፡፡

### መልመጃ አንድ

1. ድምፅ አልባ ተውኔት ምን ማለት ነው?
2. መነባነብ ምን ማለት ነው?
3. ስለ ግመል ስነ-ባህሪ ምን ተረዳችሁ?

## 2.4 ኮላዥን በአካባቢው ከሚገኝ ግብአት ተጠቅሞ ፎርሞችን፥ ለስላሳና ሸካራ ነገሮችን መስራት::

**የትምህርቱ ዝርዝር አላማ፡-**

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁበኋላ፡-

- ልዩ ልዩ ቅርፆችን፣ ፎርሞችን እንዲሁም በስዕሎች ላይ ልስላሴ እና ሻካራነትን መለየት እና መስራት ትችላላችሁ
- የተለያዩ የስዕል ስራዎች ላይ የተሰሩ የልስላሴ እና ሻካራነት ስራዎችን መለየት እና ማድነቅ ትችላላችሁ::
- የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ልዩ ልዩ የንድፍ እና የኮላዥ የፈጠራ ስራዎችን ትሰራላችሁ::

በምዕራፍ አንድ ልዩ ልዩ ቀለማት፣ ቅርጾች እንዲሁም ፎርሞችን አውቃችኋል:: በምዕራፍ ሁለት ደግሞ በይበልጥ ስለ ቅርጽ እና ፎርም ታውቃላቹ እንዲሁም እነዚህን በአንድ ላይ በማያያዝ የኮላዥ ስራን መስራት ትችላላቹ::በዚህ ምዕራፍ በተጨማሪ ስለ ልስላሴ እና ሻካራነት ትረዳላቹ:: ልስላሴ እና ሻካራነትን በኮላዥ ስራ ላይ ያለውን ሚና እንዲሁም ኮላዥን ለመስራት በምን አይነት መንገድ መጠቀም እንደምችሉ በዝርዝር ትረዳላችሁ::

የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራቹ በኋላ፦

- ስለኮላዥ በቂ ግንዛቤ እና አረዳድ ይኖራችኋል።
- ንድፍ እና ኮላዥ ለመስራት ትችላላችሁ።
- በቡድን እና በግል በአካባቢያቸው የምታገኟቸውን የተለያየ ስሪት(ልስላሴ እና ሻካራነት) እና ቀለማት ያላቸውን ቁሶች በተለያዩ ቅርፆች በመቆራረጥና በመለጣጠፍ ኮላዥ ትሰራላችሁ።

ኮላዥ የሚለው ቃል ኮል(coller) ከሚለው የፈረንሳይኛ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ማጣበቅ ፣ ማያያዝ ፣ ማገናኘት የሚሉት ናቸው። ይህ የጥበብ የፈጠራ መንገድ በዋናነት በዕይታ ጥበብ ውስጥ የሚገኝ ቢሆንም በሙዚቃም ውስጥም ይገኛል። ኮላዥ የተለያዩ ቀለማት እና ስሪቶች ያላቸውን ቁሳቁስበተለያዩ ቅርጾች በመቆራረጥ ከዛም በመገጣጠም ወይም ልዩ ልዩ ማጣበቂያዎችን በመጠቀም በማያያዝ የምንሰራው የስዕል አይነት ነው።የኮላዥስራየተጀመረውእ.ኤ.አ 1912 ሲሆን ጀማሪዎቹም ፓብሎ ፒካሶ እና ጆርጅ ብራክ ይባላሉ።በተለይ እነዚህ ሰዓሊያን ኮላዥን ኪዩቢዝም በተባለ ዘመናዊ ሥነ-ጥበብ ውስጥበብዛት ተግብረውታል። በሀገራችን ያሉ ሰዓሊያንም ኮላዥን በስዕል ስራዎቻቸውውስጥ አካተው የሚሰሩ ሲሆን ገብረክርስቶስ ደስታ የኮላዥ ስራን በተለየ ትኩረት በስዕል ስራዎቹ ውስጥ በማካተት ሰርቷል።

ኮላዥን ከመስራታችን በፊት በመጀመሪያ ኮላዥ የምንሰራውን ምስል በንድፍ ማስቀመጥ ይኖርብናል። ንድፍ ማለት አንድን ስዕል ከመስራታችን በፊት የምንሰራውን የስዕሉን አጠቃላይ የይዘት ረቂቅ በእርሳስ፣በእስክርቢቶ ወይም በቀለም በማድረግ በመስመር መስራት ማለት ነው። ሁለት አይነት የንድፍ አሰራሮች አሉ እነሱም፦

ሀ. የቀጥታ ንድፍ ለ. ሀሳባዊ ንድፍ

2.4.1 የቀጥታ ንድፍ፦ የምንለው በስዕል የምንሰራውን ነገር በዐይናችን እያየን መገልበጥ ነው::

2.4.2 ሀሳባዊ ንድፍ፦ የምንለው በሀሳባችን ውስጥ ያለውን ነገር ወደ ስዕል ስንቀይረው ነው::

በኮላዥ ውስጥ የምንጠቀማቸው ግብዓቶች የተለያዩ ቀለማት፣ ቅርፆች እንዲሁም ልስላሴና ሻካራነት ይኖራቸዋል:: በኮላዥ ውስጥ ልሳላሴና ሻካራነት የምንለው ኮላዥን ለመስራት የምንጠቀምባቸውን ግብዓቶች የገፅ ስሪት የምንለይበት ነው :: ኮላዥን ስንሰራ በልስላሴና ሻካራነት የተለያዩ ደረጃ ያላቸውን ግብዓቶች ስንጠቀም ይበልጥ ዕውነትነትን ወይም ውብትን ይጨምርልናል::

ኮላዥን ለመስራት የሚያስፈልጉን ግብዓቶች ፦

- ጠንካራ ወረቀት(ካርቶን)፣ እርሳስ፣ እስክርቢቶ፣ ከለር፣
- የተለያዩ ቀለማት እና ልስላሴና ሻካራነት ያላቸው ጋዜጣ፣ መፅሔት፣ ፎቶግራፍ ወይም ጨርቆች፣ መቀስ፣ ማጣበቂያ (ኮላ)
- ቅጠሎችን፣ ላባ፣ አበባዎችን እንዲሁም የተለያዩ ጥራጥሬዎች

ኮላዥን ለመስራት የምንከተላቸው ቅደም ተከተሎች፡-

1. ኮላዥ ለመስራት የሚያስፈልጉንን ግብዓቶች ማሟላት::

2. ኮላዥ የምንሰራበትን ካርቶን ወይም ጠንካራ ወረቀት በምንፈልገው መጠን እና ቅርፅ ቆርጦ ማዘጋጀት::

3. የምንሰራውን የኮላዥ ስራ ንድፍ ቆርጠን ባዘጋጀነው ካርቶን ላይ መሳል::

4. በመቀጠል ኮላዥ ለመስራት ያዘጋጀናቸውን ወረቀቶች ወይም ጨርቃጨርቆች በምንፈልገው መጠን እና ቅርፅ መቆራረጥ::

5. ቆራርጠን ያዘጋጀናቸውን ወረቀቶች ወይም ጨርቃጨርቆች ቀደም ሲል ቆርጠን ባዘጋጀነው ጠንካራ ወረቀት ወይም ካርቶን ላይ የሰራነውን ንድፍ ተከትለን ማጣበቂያን በመጠቀም በቦታቸው ማያያዝ።

6. በመጨረሻም የሰራነው የኮላዠ ስራ እንዲደርቅ መስቀመጥ።

7. የኮላዥ ስራን ለመስራት የምንገለገልባቸውን ቁሳቁሶች ለአደጋ ሊያገልጡ ስለሚችሉ ለመጠቀም የቤተሰቦቻችን ወይንም የመመህራን እግዛ ማግኘት ተገቢ ነው።

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ምስሎች የ ኮላዥ ምሳሌዎች ናቸው።

ምስል 1



በአራት ማዕዘንተቆርጦ የተዘጋጀ ጠንካራ ወረቀት (ካርቶን) ላይ የተሰራ የ አበባ ንድፍን አሰራት በማድረግ ወረቀቶችን በመለጣጠፍ የተሰራ ኮላዥ።

ምስል 2



በጠንካራ ወረቀት ላይ የተሰራ የቢራቢሮ ንድፍን መሰረት በማድረግ አበባና ቅጠልን በመለጣጠፍ የተሰራ ኮላዥ::





ምስል 3

ጠንካራ ወረቀትን በወፍ ቅርፅ በመቁረጥ ባለቀለም ወረቀቶችን ላባዎችን በመለጣጠፍ የተሰሩ የኮላዥ ስራዎች::



ምስል 4

ጠንካራ ወረቀት ላይ የተሰራ የአንበሳ ንድፍን መሰረት በማድረግ የተለያየ ቀለማት ያላቸውን ወረቀቶች በመለጣጠፍ የተሰራ ኮላዥ::

ምስል 5

ሀሳባዊ ንድፍን መሰረት በማድረግ በፒካሶ እና በብራክ የተሰሩ የኮላዥ ስራዎች በቅደም ተከተላቸው።

መልመጃ 1፡- ከላይ የተጠቀሰውን ቅደም ተከተል እንዲሁም ምሳሌዎቹን መሰረት በማድረግ የቤት ስዕል በኮላዥ ሰርታችሁ አሳዩ።

መልመጃ 2፡- ሀሳባዊ ንድፍን መነሻ በማድረግ የራሳችሁን ስዕል በኮላዥ ሰርታችሁ አሳዩ።

መልመጃ 3

1. ንድፍ ምንድን ነው? በስንት ይከፈላል?
2. ኮላዥ ምንድን ነው?
3. የኮላዥ ስዕል ጀማሪዎች እነማን ናቸው?

### 2.4.3 ፎርም እና ስሪት (ልስላሴ እና ሻካራነት)

በምዕራፍ አንድ ስለ ፎርሞች በተወሰነ መልኩ ተምራችኋል። በተጨማሪም በምዕራፍ ሁለት ልስላሴና ሻካራነትን በኮላዥ ውስጥ አይታችኋል። በዚህ ንዑስ ርዕስ ውስጥ ደግሞ ስለፎርም እንዲሁም ስለልስላሴና ሻካራነት በጥልቀት እንማማራለን። በተጨማሪ የተለያዩ ፎርሞችን በስዕል እና በቅርፃ ቅርፅ መልክ ትሰራላቹ። ልስላሴና ሻካራነትን በስዕል መስራትን ትለማመዳላቹ።

**የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

- ፎርሞች በስዕል ውስጥ ያላቸውን ጠቀሜታ ትረዳላችሁ
- የፎርሞችን ልዩነት እና ባህሪያት ትገነዘባላችሁ
- በአካባቢያቹ የሚገኙ ግብዓቶችን በመጠቀም የተለያዩ የፎርም ቅርፃ ቅርፆችን ትሰራላችሁ
- ልስላሴና ሻካራነትን በስዕል ላይ ያለውን ሚና ትረዳላችሁ


### 2.4.4 ፎርም


ፎርም የሚለውን ቃል በሁለት የተለያዩ መንገዶች ልንረዳው እንችላለን። የመጀመሪያው አንድ ሰዓሊ የሥነ-ጥበብ መሰረታዊያንን የሚጠቀምበት እና የሚያስቀምጥበት መንገድ ነው።ይህም የስዕል ስራን አጠቃላይ አቀማመጥ የስዕሉ ፎርም ብለን እንጠራዋለን። ሁለተኛው ደግሞ ሶስት አውታረ መጠን ያለው እና ቦታን የሚይዝ ቁስ ፎርም ብለን እንጠራዋለን። ፎርም እንደ ቅርጽ ርዝመት እና ስፋት ያለው ሲሆን ከቅርጽ የሚለየው ፎርም ጥልቀት አለው። ርዝመት፣ ስፋት እና ጥልቀት ሶስት አውታረ መጠን በመባል ይታወቃሉ። ፎርም በተለይም በቅርፃ ቅርፅ ስራ ውስጥ እጅግ ጠቃሚ ሲሆን የምንሰራውን የቅርፅ ስራ መሰረታዊ በሆኑ ፎርሞች በመጀመር አጠቃላይ ይዘትን ቀላል በሆነ መንገድ ማስቀመጥ ያስችለናል። ይህም ቀጣይ በቅርፃ ቅርፆች ላይ ለምንሰራቸው ረቂቅ ስራዎች እንደ መሰረት እንገለገልበታለን። ፎርም ጂኦሜትሪያዊ ወይንም ልቅ ሊሆን ይችላል። ጂኦሜትሪያዊ ፎርም የሚባሉት ሂሳባዊ ልኬት ያላቸው እንደ ኪዩብ፣ ኮን፣ ሲሊንደር፣ የመሳሰሉት ናቸው። እነዚህን የፎርም አይነቶች እርስ በእርስ በተለያየ መንገድ በማገናኘት ተጨማሪ ጂኦመትሪያዊ ይዘቶችን ማግኘት እንችላለን።

ፎርሞች እንደ ቀለማት እና ቅርፆች የየራሳቸው ባህሪ ሲኖራቸው የራሳቸው የሚወክሉትም ነገር አላቸው። እንደምሳሌ ብንወስድ ፒራሚድ ጥንካሬን ይገልፃል። ይህም ማለት አንድ ቁስ ጠንካራ ባይሆንም እንኳን ፎርሙ የፒራሚድ ከሆነ ለአይናችን ጠንካራ መስሎ ይታየናል። ኪዩብ ደግሞ ክብደትን ይገልፃል። ይህም ማለት አንድ የኪዩብ ፎርም ያለው ቁስ ቀላል ቢሆንም እንኳን ለዐይናችን ስናየው ከባድ መስሎ ይታየናል።


በአካባቢያችን የሚገኙ ጂኦሜትሪያዊ ፎርም ያላቸው ነገሮች ለምሳሌ፡- ጠመኔ ሲሊንደር፣ዳስተር ባለ አራት ማዕዘን ፕሪዝም እንዲሁም ኳስ ሉላዊ ፎርም አላቸው።


ከዚህ በታች በምስሉ ላይ የተጠቀሱት ጂኦሜትሪያዊ የፎርም ዕይነቶች ናቸው








❖ ጂኦሜትሪያዊ ፎርሞችን እርስ በርስ በማገናኘት የሚሰሩ፡፡









❖ በአካባቢያችን የሚገኙ ልቅ ፎርም ያላቸው ነገሮች ለምሳሌ ድንጋይ፣ደመና፣ ዛፍ የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ከዚህ በታች ምስል የምንመለከተው ልቅ ፎርሞችን ነው፡፡



ፎርምን ማወቅ በስዕል ስራ ውስጥ ያለው ጠቀሜታ እጅግ ከፍተኛ ነው:: በተለይ በቀጥታ የንድፍ ስራ ላይ በአካባቢያችን የምንመለከታቸውን ቁሳቁስ ለመሳል የፎርም መሰረታዊ ዕውቀት ሊኖረን ይገባል:: ከዚህ በታች በምንመለከተው በቁሳቁስ ጥናት ስዕሎች ላይ የተለያዩ ፎርሞችን እንመለከታለን::






ከዚህ በታች በተቀመጡት ምስሎች የምንመለከተው በጠንካራ ወረቀት የተሰሩ ፎርሞችን ነው::









መልመጃ 1 ፦ መምህራችሁ በክፍል ውስጥ ያስቀመጡላችሁን ጂኦሜትሪያዊ ፎርም ያለዉን ቁስ በመመልከት የቀጥታ ንድፍ ስሩ::

መልመጃ 2፦ ሁለት የተለያዩ ጂኦሜትሪያዊ ፎርሞችን በመጠቀም የቅርፃ ቅርፅ ስራ ሰርታችሁ አሳዩ::

መልመጃ 3፡-

1. ጂኦሜትሪያዊ ፎርም የሚባሉት ምንድን ናቸው? 5 ምሳሌዎችን ስጡ፡፡

2. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ጂኦሜትሪያዊ እና ልቅ ፎርም ያላቸውን ነገሮች ዘርዝሩ፡፡

### 2.4.5 ልስላሴ እና ሻካራነት

የአንድን ቁስ ገፅ በመመልከት እና በመዳሰስ ስሪቱን ለስላሳ፣ስስ፣ጠንካራ፣ ፀጉራማ፣ አንሸራታች፣ ከርዳዳ፣ የሚያሟልጭ በማለት እንገልፃቸዋለን፡፡ የአንድን ቁስ ገፅ ስሪት በመመልከት እና በመዳሰስ የምናገኘው የጥራት ደረጃ የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት የአንድን ቁስ ገፅ ስሪት በሁለት ዓይነት መንገድ ልንረዳ እንችላለን፡፡

ሀ. አካላዊ የስሪት(ልስላሴ እና ሻካራነት) አረዳድ፦ በዚህ የአረዳድ መንገድ የቁሱን ገፅ በእጃችን በመዳሰስ ስሪቱን ማወቅ እንችላለን፡፡ይህ የአረዳድ መንገድ የቁሱን የገጽ ስሪት በትክክል የምናውቅበት ነው፡፡


ለ. የእይታ የስሪት(ልስላሴ እና ሻካራነት) አረዳድ፦ ይህ የአረዳድ መንገድ የቁሱን ገፅታ በዐይናችን በማየት ብቻ ስሪቱን ለማወቅ የምንሞክርበት መንገድ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ይህንን የአረዳድ መንገድ ብቻ ተጠቅመን የአንድን ቁስ ገፅታ ስሪት በትክክል መወሰን ወይም ማወቅ ይከብዳል፡፡

ለምሳሌ፦ ስንመለከተው ለስላሳ መስሎ የታየን ገፅ በምንዳስሰው ጊዜ ሸካራ ሊሆን ይችላል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ስንመለከተው ሻካራ የመሰለንን ገፅ ለስላሳ ሆኖ ልናገኘው እንችላለን፡፡

በዕይታ ልስላሴን እና ሻካራነትን ለማሳየት የተለያዩ የስዕል አሰራር መንገዶች ሲኖሩ ለምስሌ ፡-የተለያየ የልስላሴ እና ሻካራነት ይዘት ያላቸውን እንደ ቅጠል፣ ሳንቲም፣ ቁልፍ፣ ልዩ ልዩ በላያቸው ላይ ፅሁፍ ውይም ስዕል የተቀረፀባቸው ነገሮች ላይ ወረቀትን በማስደገፍ ወረቀቱን በእርሳስ ወይም በከለር በማሸት በነገሮቹ ላይ የሚታየዉን ምስል ወደ ወረቀቱ መገልበጥ ይቻላል፡፡

ልስላሴ እና ሻካራነት በስዕል ስራ ውስጥ ብዙ አይነት አገባብ ወይም ጥቅም አለው:: አንድን ንድፍ በምንሰራበት ወቅት የምንሰራው ቁስ ምን አይነት የልስላሴ እና ሻካራነት ጠባይ እንዳለው ስናሳይ የምንሰራው የንድፍ ስራ ወደ እውነታ የቀረበ እንዲሆን ያደርገዋል:: በተጨማሪም የምንሰራው የስዕል ስራ ውስጥ ልስላሴ እና ሻካራነትን ማሳየት ስንችል ስዕሉ ተጨማሪ ውበት እንዲኖረው እናደርጋለን::

ከዚህ በታች በቀረበው ስዕል ላይ የተለያዩ የልስላሴ እና ሻካራነት ደረጃዎችን መመልከት እንችላለን::


መልመጃ 4፡_የተለያይ የልስላሴ እና ሻካራነት ይዘት ያላቸው ቁሶች ላይ ወረቀት አስደግፋችሁ በእርሳስ በማሸት የቁሱን ልስላሴ እና ሻካራነት በወረቀቱ ላይ እንዲታይ አድርጉ::

መልመጃ 5

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ቁሶችን እና የገፃቸውን ስሪት ዘርዝሩ::
2. ልስላሴ እና ሻካራነት በስዕል ዉስጥ ያለውን ጠቀሜታ ግለፁ::

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ሙዚቃ ለመፃፍ አስፈላጊ የሆኑትን የሙዚቃ መፃፍያ ምልክቶችን በዋነኝነት ሰታፍና ክሌፎችን አውቀችኋል፡፡ እነዚህም ምልክቶች በጣም ወሳኝና የሙዚቃ ድምፆችን የሚወስኑ በመሆናቸው መስመሮቹንና ክፍት ቦታዎቹን ከክሌፍ ምልክት ጋር ያላቸውን ውክልና በደንብ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡

ኮላዥ ኮል ከሚል የፈረንሳይ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ማያያዝ፣ማጣበቅ የሚል ነው፡፡ ኮላዥ ማለት የተለያዩ ወረቀቶችን፣ ጨርቆችን፣ ቅጠሎችን ቆራርጦ በመለጠፍ የሚሰራ ስዕል ነው፡፡ ፎርም የምንለው የአንድን ስዕል አጠቃላይ ይዘት ወይም ባለሦስት አውታረመጠን ቅሶችን ነው፡፡ ፎርምን ማወቅ የቅርጻቅርጽ ስራዎችን ቀላል በሆነ መንገድ ለመስራት ያስችላል፡፡ ልስላሴ እና ሻካራነት የሚባለው በተለያዩ ቁሶች ገጽ ላይ የሚገኝ በማየት ወይም በመዳሰስ የምንለየው ነው፡፡ በስዕል ላይ ልስላሴ እና ሻካራነትን መስራት ስንችል የምንሰራውን ስዕል እውታነት ማሳየት እንችላለን፡፡

## ማጠቃለያ ምዘና፡-

፩. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ምረጡ፡፡

1. በስታፍ የመጀመሪያ ክፍል ላይ የሚቀመጥ እና የሙዚቃ ድምፆችን ለመለየት የሚያስችል ምልክት የቱ ነው፡፡

   ሀ. ክሌፍ　　　ሐ. ቤዝ
   
   ለ. ስታፍ　　　መ. ትሬብል

2. የG (ጂ) ድምፅ ከሁለተኛው መስመር የሚጀምርበት የክሌፍ አይነት የቱ ነው፡፡

   ሀ. ክሌፍ　　　ሐ. ጂ (ትሬብል) ክሌፍ
   
   ለ. ስታፍ　　　መ. ቤዝ ክሌፍ

3. የ F (ኤፍ) ድምፅ ከአራተኛው መስመር የሚጀምርበት የክሌፍ አይነት የቱ ነው፡፡

ሀ. ክሌፍ
ለ. ስታፍ
ሐ. G ጂ (ትሬብል) ክሌፍ
መ. F (ኤፍ) ወይም ቤዝ ክሌፍ

4. ይህ የተቀመጠው ምስል የትኛውን የክሌፍ አይነት ይወክላል፡፡



ሀ. F (ኤፍ) ክሌፍ
ለ. G (ጂ) ወይም ትሬብል ክሌፍ
ሐ. ስታፍ
መ. C (ሲ) ክሌፍ

5. ከታች የተቀመጠው ምስል የትኛውን የክሌፍ አይነት ይወክላል፡፡



ሀ. F (ኤፍ) ክሌፍ
ለ. G (ጂ) ወይም ትሬብል ክሌፍ
ሐ. ስታፍ
መ. C (ሲ) ክሌፍ

6. G (ጂ) ወይም ትሬብል ክሌፍ መስመር ላይ ያሉ ድምፆች የትኞቹ ናቸው

ሀ. E G B D F
ለ. G B D F A
ሐ. F A C E
መ. A C E G

7. F (ኤፍ) ክሌፍ ክፍት ቦታዎች ላይ ያሉ ድምፆች የትኞቹ ናቸው

ሀ. E G B D F
ለ. G B D F A
ሐ. F A C E
መ. A C E G

8. F (ኤፍ) ክሌፍ መስመር ላይ ያሉ ድምፆች የትኞቹ ናቸው

ሀ. E G B D F
ለ. G B D F A
ሐ. F A C E
መ. A C E G

9. G (ጂ) ወይም ትሬብል ክሌፍ ክፍት ቦታዎች ላይ ያሉ ድምፆች የትኞቹ ናቸው

ሀ. E G B D F        ሐ. F A C E
ለ. G B D F A        መ. A C E G

10. የኮላዥ ስራ የተጀመረው በስንት ዓመተምህረት ነው?

ሀ. 1800    ለ. 1912    ሐ. 2000    መ. 1712

11. በሀገራችን ኮላዥን በመስራት የሚታወቀው ሰዓሊ ማን ይባላል?

ሀ. አፈወርቅ ተክሌ    ለ. ገብረክርስቶስ ደስታ
ሐ. ወርቁ ማሞ    መ. ሁሉም

12. ንድፍ የምንለው በስንት ይከፈላል?

ሀ. 2    ለ. 4    ሐ. 3    መ. 5

13. ፎርም የሚለውን ቃል በስንት አይነት መንገድ ልንረዳው እንችላለን?

ሀ. በ3    ለ. በ5    ሐ. በ1    መ. በ2

14. ልስላሴ እና ሻካራነትን የምንረዳበት መንገድ የሆነው ከሚከተሉት የትኛው ነው?

ሀ. በማየት    ለ. በመዳሰስ    ሐ. በመሳል    መ. ሀ እና ለ

# ምዕራፍ ሦስት

## ታሪካዊና ባህላዊ አውዶች

### መግቢያ

ጥበብ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ሚና አለ የማይባል ነው ይህም የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ከጥበባዊ ስራ ተለይቶ ያውቃል ማለት አስቸጋሪ ነው፡፡ ጥበብ የባህል፡ የታሪክ እና የሀይማኖት መገለጫ ነው፡፡ ስለዚህ ጥበብን ከማህበረሰብ ማህበረሰብን ከጥበብ ለይቶ ማየት አስቸጋሪና የማይቻል ነው፡፡

### አጠቃላይ የመማር ውጤት

- ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቁ በኋላ ጥበብ በማህበረሱ ውስጥ ያለውን ፋይዳ ትረዳላችሁ፡፡
- ያለፈውንና የአሁኑን የክወናና ዕይታ ጥበባት ትረዳላችሁ፡፡
- ስለ አገራዊ የሆኑ ታሪካዊ ቦታዎች ታውቃላችሁ፡፡

## 3.1 ሙዚቃ በማኅበረሰብ ውስጥ ያለው ጠቀሜታ

ጥበብ በማህበረሰብ ውስጥ ያለው ጠቀሜታ በብዙ መንገድ የሚገለፅ ሲሆን የማህበረሰቡ አጠቃላይ የአኗኗር ሁኔታ ነፀብራቅ ነው፡፡ ጥበብ የአንድ ሀገር ባህላዊ ፤ ማህበራዊ ፤ ታሪካዊ ፤ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ነባራዊ ሁኔታዎች መግለጫና መገለጫ ነው፡፡

**የትምህርቱ ዝርዝር አላማ፡-**

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ሙዚቃ በማህበረሰብ ውስጥ ከባህል አንፃር ያለውን ጥቅም ትረዳለችሁ፡፡
- ሙዚቃ በማህበረሰብ ውስጥ ከታሪክ አንፃር ያለውን ጥቅም ትረዳላችሁ፡፡

ኢትዮጵያ ከትውልድ ወደ ትውለድ ሲተላለፍ በመጣ ጠንካራ የታሪክ ፤ የባህል እና የሀይማኖት መሰረት ላይ የቆመች ሀገር ናት፡፡ ባህል የሚፈጠረው አንድ ማህበረሰብ አብሮ በመኖር እርስበእርሱ በሚያደርገው ግንኙነት አማካኝነት

ነው፡፡ ሙዚቃ ፤ ዳንስ ፤ ቋንቋ ፤አለባበስ፤ አመጋገብ ፤ የመሳሰሉት የባህል ዋና ዋና ክፍሎች ሲሆኑ በተለይም ሙዚቃ በማህበረሰቡ ውስጥ የሰዎችን ስሜት ከመግለፅ አልፎ በተማሪዎች የአእምሮ እድገት ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡


በተጨማሪም መዚቃ የአንድን ማህበረሰብ ባህላዊ ፣ታሪካዊ እና መንፈሳዊ ትስስርን በማሳደግ ሰዎች ወደ አንድ ህብረት እንዲመጡ ያግዛል ፡፡በመሆኑም ሁሉም ማህበረሰብ ሙዚቃን በየጊዜው ለሚፈጠሩ ጉዳዮች ለምሳሌ ለሀዘን ለሰርግ፣ለደስታ፣ ለትካዜ፣ ለስራ፣ ለጦርነት፣ ለጀግንነት ፣ለአደን፣ እና ለመንፈሳዊ አገልግሎቶች ይጠቀምባቸዋል፡፡

ከዚህ ቀጥሎ የተወሰኑትን ዘፈኖችና በማህበለሰቡ ውሰጥ ምን አይነት ግልጋሎት እንደሚሰጡ እናያለን፡፡

3.1.1 የጦርነት ዘፈኖች፡- ሙዚቃ የሰዎችን ስሜት የመቆጣጠር እና የማነሳሳት ኃይሉ ከፍተኛ በመሆኑ ለጦርነት የሚዘፈኑ ዘፈኖች በጦር ሜዳ የሚዋጋውን አርበኛ፣ ተዋጊ ወይም ወታደር ወኔ በመቀስቀስ በከፍተኛ ሞራል እንዲዋጋ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ሽለላ፣ ፉከራ ፣ቀረርቶ እና ፋኖ ፋኖ የሚባሉት የጦርነት ዘፈኖች ውሰጥ የሚመደቡ ናቸው፡፡

3.1.2 የለቅሶ ዜማዎች፡- ሰዎች በእለት ከ እለት እንቅስቃሴ ውስጥ በሚገጥማቸው ሀዘን ምክንያት የሚዘፈኑ ዘፈኖች ናቸው፡፡ ሙሾ እና የሀዘን እንጉረጉሮ በለቅሶ ዘፈን ውስጥ የሚመደቡ ናቸው፡፡

3.1.3 የሕፃናት ዘፈኖች ፡- እሹሩሩ ይህ ዘፈን የህፃናት ማባበያ ዘፈን ሲሆን ህፃናት በጨቅላ እድሜያቸው ሰላማዊ ስሜት ተሰምቷቸው እንቅልፍ እንዲተኙ በአብዛኛው በእናቶች የሚዘፈን ነው፡፡






ምስል 1፡- ሕፃናትን አባብሎ ማስተኛት (እሹሩ ሩሩሩ)

ሕፃናት በአንድነት ተሰባስበው ሲጫወቱ የሚዘፈኑ እና በማህበረሰቡ የተፈጠሩ ብዙ የህፃናት ዝማሬዎች (ዘፈኖች) አሉ፡፡ ከዚህም ውስጥ አንዱ ጨረቃ ድንቡል ቦቃ የሚለው ይገኝበታል፡፡

ምሳሌ፡- ጨረቃ ድንቡል ቦቃ በኖታ ላይ ሲፃፍ



<u>ጨረቃ ድንቡል ቦቃ ግጥም</u>

ጨረቃ ድንቡል ቦቃ

አጤ ቤት ገባች አውቃ

አጤ ቤት ያሉ ልጆች

ፈተጉ ፈታተጉ


በቁንቢት አስቀመጡ


ቁንቢቷ ብትሰበር በዋንጫ ገለበጡ

አጃ ቆሎ ስንዴ ቆሎ

ያችን ትተሽ ይቺን ቶሎ

**በሚከተለው መሰረት ጨረቃ ድንቡል ቦቃን በሩብ እና በግማሽ ኖታ ተለማመዱ::**






**መልመጃ 1፡-** የሚከተሉትን ጥቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ

1. ከሚከተሉት ውስጥ በጦርነት ወቅት አርበኛን ለማነቃቃት የምንጠቀምበት የዜማ አይነት የቱ ነው፡፡

   ሀ. ጨረቃ ድንቡል ቦቃ     ሐ. ሽለላ

   ለ. ፉከራ     መ. ለ እና ሐ

2. እናቶች ህፃናቶችን ለማስተኛት የሚጠቀሙበት ዜማ የቱ ነው

   ሀ. ፉከራ     ሐ. እሹሩሩ

   ለ. ጨረቃ ድንቡል ቦቃ     መ. ፋኖ

3. በማህበረሰቡ ውስጥ በለቅሶ ጊዜ የሚጠቀሙበት ዜማ አይነት ምን ይባላል፡ ፡

   ሀ. ሙሾ     ሐ. ፋኖ

   ለ. እሹሩሩ     መ. ቀረርቶ

መልመጃ 2፡- የሚከተሉትን የጨረቃ ግጥም በባዶ ቦታው ላይ የጎደሉትን አሟሉ፡፡

1. ጨረቃ ድንቡል ቦቃ .................. ገባች አውቃ
2. አጼ ቤት ያሉ ልጆች....................በቁንቢት አስቀመጡ
3. ቁንቢቷ ብትሰበር.......................ገለበጡ፡፡

### 3.1.4 ሙዚቃ በማህበረሰብ ውስጥ ከታሪክ አንፃር ያለው ሚና

ታሪክ የአንድን ማህበረሰብ ያለፈውን አጠቃላይ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ እና መንፈሳዊ ገፅታን የሚያሳየን መነፅር ነው፡፡ስለሆነም ሙዚቃ ከአንድ ሃገር ህዝብ ታሪክ ጋር ያለው ትስስር ከፍተኛ ነው፡፡

ምሳሌ ለመጥቀስ የአደዋ ድል ኢትዮጵያውያን በአንድነት ተባብረው ከጭቆና ነፃ የወጡበት እና በአለም ላይ የተጨቆኑ ህዝቦች የነፃነት ችቦ የለኮሱበት ድል ነው፡ ፡ በዚህ የአደዋ ጦረነት ላይ ሙዚቃ የነበረው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነበር፡፡
አዝማሪዎች በአድዋ ጦርነት ወቅት የአርበኞችን ሞራል በማነቃቃት እና በማበረታታት ጦርነቱ በኢትዮጵያ አሸናፊነት እንዲጠናቀቅ ከፍ ያለ ሚና ተጫውተዋል፡፡ ምሳሌ፡- በመፎከር፣ በመሸለል፣ በማቅራራት
ጣልያን ኢተዮጵያን ቅኝ ለመግዛት ባካሄደው የአምስት አመት ጦርነት አርበኞችን በማነሳሳታቸው ብቻ በርካታ አዝማሪዎችን ገድሏል፡፡ አዝማሪዎች ግጥምን ከዜማ ጋር በማዋሃድ እንዲሁም በመሰንቆ በመታጀብ ለማህበረሰቡ የሚሰጡት ጥቃም ከፍተኛ ነው፡፡



ምስል 3፡- አዝማሪዎች ከማሲንቆ (መሰንቆ) ጋር

ሙዚቃ በማህበረሰብ ውስጥ መንፈሳዊ አገልግሎትን በመስጠት ሰዎች ሃይማኖታዊ አምልኮ የሚያከናውኑበት አንዱ የጥበብ ክፍል ነው።
ኢትዮጰያዊው የሙዚቃ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በ 505 ዓመተ ምህረት በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ከእናቱ ክርሰቲና (ታውክሊያ) እና ከአባቱ ይስሀቅ (አብድዩ) በአክሱም ጽዮን የተወለደ ሲሆን ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚውሉ ዜማዎችን በሶስት ወፎች አማካኝነት ከሰማየ ሰማያት እንደተቀበለ ታሪክ ያስረዳናል። ቅዱስ ያሬድ ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚውሉ ሶስት አይነት ዜማዎች አሉት። እነርሱም ግዕዝ፤ እዝል ፤ አራራይ ይባላሉ።




ምስል 4፡- የቅዱስ ያሬድ ምስል

## 3.2 የውዝዋዜ ጥበብ በማህበረሰቡ ውስጥ ከባህልና ከታሪክ አንፃር

ባህል የአንድ ማህበረሰብ  እሴት መገለጫ ከሆኑ መንገዶች መካከል አንዱ

ነው። አንድ ማህበረሰብ ከሌላ ማህበረሰብ የሚለየው በቋንቋ፡ አመጋገብ ስርዓት፡ በአለባበስ፡ በቤት አሰራር፡ በእምነት፡ እና በሌሎች ልዩ ልዩ በሆኑ ጉዳዮች አንዱ ከአንዱ ይለያል። ኪነ ጥበባዊ ከሆኑ ጉዳዮች ማለትም በውዝዋዜ አንዱ ከሌላው ራሱን የሚገልጽበት መንገድ ይለያል።

## ዝርዝር አጥጋቢ የመማር ውጤት

- በሚና ጨዋታ፡ ውዝዋዜ እንዲሰሩ ማድረግ፡፡

ውዝዋዜ የአንድ ማህበረሰብ ታሪክ መገለጫ ተደርገው ከሚወሰዱ ኪነ-ጥበባዊ ድርጊቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ አገራችን ኢትዮጵያ ከሰማንያ በላይ ብሔረሰብ ያላት ትልቅ እና የስልጣኔ መገለጫ ከሆኑ ቀደምት አገራት አንዷ ነች፡፡ በዚህች ትልቅ አገር ማህበረሰቡ እንደ ራሱ ታሪክ፡ ባህል፡ ወግ፡ ልማድ፡ አስተሳሰብ እና መልካምድራዊ አቀማመጥ የራሱ የሆነ ስሜቱን እና ማንነቱን በዳንስ ወይም ውዝዋዜ ሲገልጽ ኖሯል ወደፊትም ይሄ ድርጊት ይቀጥላል፡፡ ውዝዋዜ የአገራችን ኢትዮጵያ ልዩ ከሆኑ መገለጫዎቿ እና አገር በቀል ከሆኑ ክዋኔ ጥበባት መካከል ይመደባል፡፡ በአገራችን ከሚገኙ ባህላዊ ውዝዋዜዎች መካከል ከዚህ ቀደም የተወሰኑትን የውዝዋዜ አይነቶች ተመልክተናል፡፡

ውዝዋዜ እንደ ማህበረሰቡ ባህል እና ትውፊት የሚቀርብበት መንገድ

ይለያያል፡፡ በሀዘን ወቅት የሚደረግ የውዝዋዜ አይነት፡ በደስታና በሰርግ ጊዜ የሚደረግ የውዝዋዜ አይነት፡ በጦር ሜዳ ወይም ህብረተሰቡን ለመቀስቀስ የመሚደረጉ የውዝዋዜ አይነቶች እንደ አካባቢው ማህበረሰብ ይለያያል፡፡

ለምሳሌ፡-

- ጉራጊኛ ባህላዊ ውዝዋዜ፣ የሶማሌ ባህላዊ ውዝዋዜ፣ የአማራ ባህላዊ ውዝዋዜ፣ የኦሮሞ ባህላዊ ውዝዋዜ፣ ትግርኛ ባህላዊ ውዝዋዜ፣ የወላይትኛ ባህላዊ ውዝዋዜ…ወዘተ፡፡

### 3.3 የትያትር ጥበብ በማህበረሰቡ ውስጥ ከባህልና ከታሪክ አንፃር ያለው ሚና

ጥበብ የባህል፡ የታሪክ እና የሀይማኖት መገለጫ ነው፡፡

3.3.1 ከእምነት አንፃር፡- በሀገራችን ኢትዮጵያ በርካታ እምነቶች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ሀይማኖታዊ ቦታዎች ውስጥ የስዕል፣ ቅርጻ ቅርጽ፣ ዜማ፣ ስነ ጽሁፍ ፈጣሪን ለማመስገኛነት የሚጠቀሙባቸው ጥበባዊ ስራዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ጥበባዊ ስራዎች ኢትዮጵያዊ የሆኑ አገር በቀል እውቀቶች ናቸው፡፡

3.3.2 ከባህል አንፃር፡- ባህል የሰው ልጅ በተፈጥሮ የማያገኛቸውን ነገሮች ከቤተሰቡ እና ከማህበረሰቡ የሚያገኝባቸው ወይም የሚወርሳቸው መገለጫዎች ናቸው፡፡ የሰው ልጅ ችግሮቹን ለመፍታት ከድሮ ጀምሮ ብዙ ጥበባዊ ስራዎችን ሰርቷዋል፤ ለምሳሌ፡-

እሳት ፡- የሰው ልጅ በችግሩ ጊዜ ድንጋዮችን በማፋጨት እና በተለያየ መንገድ እሳትን በመፍጠር የሚመገባቸውን ምግቦች ለማብሰል እና ለሙቀት እንዲሁም በጨለመም ጊዜ ለብርሃንነት ይጠቀሙበት ነበር፡፡

ስለታማ ነገሮች፡- ስለታማ ነገሮች የተፈጠሩት እንዲሁ የሰው ልጅ ለአደን በሚወጣበት ጊዜ በቀላሉ የሚያድነውን እንስሳ ለመያዝ እና ቆራርጦ ለመመገብ እንዲሁም እራሱን ከተለያዩ አደገኛ ጉዳት ከሚያደርሱ አራዊት ለመጠበቅ ሲል ስለታማ ነገሮችን ፈጥሩዋል፡፡

ስለዚህ ጥበባዊ ስራዎች የሰው ልጅ ዕለት ከእለት የሚያጋጥሙትን ችግሮች ለመፍታት የሚያድርገው የፈጠራ ውጤት ነው፡፡ ይህም ችግሮች ላይ ብቻ ሳይወሰን ራሱን ለማዝናናት ሙዚቃ፤ስዕልና ትያትር ሌሎች ኪነጥበባዊ ስራዎችንም ጨምሮ አእምሮን ለማፍታታት እና እውቀት ለማስጨበጥ አይነተኛ የማህበረሰቡ መገለጫዎች ናቸው፡፡ ጥበብ በተለያየ መንገድ ሊገለጽ ይችላል፡ ጥበብ በሰው ልጅ ግብርነታቸው፤የሰው ልጅ መከሰቻ በመሆናቸው ለማህበረሰቡ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ጉልህ ነው፡፡

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን የፊታውራሪ ተ/ኃዋርያት ተ/ማርያም ስንኝን በማጥናት በመነባበብ መልክ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡ የንባብ ባህላችሁ ይዳብራል የፈጠራ አቅማችሁ ይጨምራል፡፡

**ዝንጀሮና መስተዋት**

አንድ ቀን ዝንጀሮ እያመነታታች፣
ጌጥ እገዛ ብላ ከመደብር ገባች፡፡
ሰፋሪ መስተኖት የጠራ ያመራ፣
ከመጀብር ውስጥ ተሰቅሎ ነበረ፡፡
መለስ ቀለስ ብላ እቃ ስታማርጥ፣
መልኳን አገኘችው ከመስተዋቱ ውስጥ፡፡
ኋላም በመደነቅ እንዲህ ተናገረች፣
ወደ መስተዋቱ ትኩር ብላ እያየች፡፡
አረገኝ ይህቺ ምንድነች እንዲህ ያለች ፍጥረት
አጉል የተሰራች ሰው አይሉዋት አውሬ
ላስተያየቱም እንኳ ጥቂት የለው እፍረት፡፡
አይቻትም አላውቅ እኔስ ያለዛሬ፡፡
እንዴት ያስቀይማል የደረትዎ ቅላት
ከኸረት ዋስ በታች ደግሞ ምን ጠበሳት
ምነው በቀረችው ጥንቱን ስትፈጥር፣
እኔስ እሷን ብሆን ታንቄ እሞት ነበር፡፡
አሁን በዝንጀሮ ምን ያስተርተኛል
መልኩን የሚያራክስ ምን ፍጡር ይገኛል፡፡

መልመጃ 1

1. ከዝንጀሮ ታሪክ ምን ተማራችሁ፡፡

## 3.4 የዕይታ ጥበብ በማሕበረሰብ ውስጥ ከባህል እና ከታሪክ አንፃር ያለው ሚና

የዕይታ ጥበብ በአንድ ማኅበረሰብ ባህል እና ታሪክ ውስጥ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ የዕይታ ጥበብ ባህልን ለማስተዋወቅ እና ታሪክንም ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ ይጠቅማል፡፡ በዚህ ምዕራፍ የተለያዩ በሀገራችን ያሉ ታሪካዊ ቦታዎችን ስነ-ጥበባዊ ይዘት እንቃኛለን፡፡ እንዲሁም በሃገራችን ያሉ የተለያዩ የባህል አልባሳትን እና ጌጣጌጦችን እናያለን፡፡

የምዕራፉ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ

- በሀገራችን ያሉ የተለያዩ ታሪካዊ የስነ-ጥበብ ቦታዎች እና ስራዎችን ታውቃላችሁ
- የተለያዩ ባህላዊ አልባሳት ፣ ጌጣጌጦች እና የእጅ ስራዎችን ታውቃላችሁ
- የጓደኞቻችሁን እና የቤተሰቦቻችሁን የልብስ ቀለማት ማወቅ እና መግለፅ ትችላላችሁ
- የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ ቀለማትን ትርጓሜ ታውቃላችሁ

### 3.4.1 የዕይታ ጥበባት በማኅበረሰብ ውስጥ ከባህል አንፃር ያላቸው ሚና

ባህል ማለት የአንድ ማኅበረሰብ እሴት ሲሆን ይህም የአመጋገብ ስርዓትን፣ የአለባበስ ስርዓትን ፣ የአምልኮ ስርዓትን፣ የቤት አሰራርን የመሳሰሉትን በአንድ ላይ ጠቅልሎ የሚይዝ ነው:: የዕይታ ጥበባት ባህልን ለማስፋፋት ፣ ለትውልድ ጠብቆ አማቆየት እንዲሁም ለማስተዋወቅ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አላቸው:: እንደሚታወቀው በሀገራችን ብዙ ብሔረሰቦች ይገኛሉ እነዚህም ብሔረሰቦች የየራሳቸው ባህል እና መገለጫዎች አሏቸው:: እነዚህን ባህሎቻቸውን የዕይታ ጥበባትን በመጠቀም አስፋፍተዋል፣ አስተዋውቀዋል እንዲሁም ከትውልድ ወደ ትውልድ አስተላልፈዋል:: በዚህ ክፍልም በሀገራችን ያሉ የተለያዩ የባህል አልባሳትን እናያለን ቀለሞቻቸውንም እናውቃለን:: በተጨማሪም የተለያዩ ጌጣጌጦችን እና የዕደ-ጥበብ ውጤቶችንም በስፋት እንቃኛለን::

ከላይ እንደጠቀስነው አልባሳት የባህል አንድ አካል ናቸው:: በሀገራችን የሚገኙ የልዩ ልዩ ብሄረሰቦች አልባሳት የየራሳቸው የሆነ ቀለም፣ ሐረግ፣ ጥለት እና የአስራር መንገድ ያላቸው ሲሆን እነዚህም የዕይታ ጥበብ መገለጫዎች ናቸው:: የባህል አልባሳትን በመልበስ ብቻ ለተመልካች ሃገርን እና ባህልን በቀላሉ ማስተዋወቅ እንችላለን::

ከዚህ በመቀጠል የቀረቡት ምስሎች በሀገራችን የሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች አልባሳት፣ የሸክላ ስራዎች፣ ጌጣጌጦች፣ እንጨት ስራዎች እንዲሁም የቅርጫትና ሠፌድ ስራ ውጤች ናቸው::

ባህላዊ አልባሳት















ከአልባሳት በተጨማሪ በሀገራችን የሚገኙት ሌሎች የዕደ-ጥበብ ውጤቶች እንደ ጌጣጌጥ፣ የሸክላ ስራ ውጤቶች፣ የእንጨት ስራ ውጤቶች ፣ልዩ ልዩ የቅርጫት ስራዎች የመሳሰሉት የባህል መገለጫ የዕይታ-ጥበብ ውጤቶች ናቸው፡፡ በመቀጠልም ከእነዚህ የዕይታ ጥበባት መካከል የተወሰኑትን እንመልከት፡፡

## የሸክላ ስራዎች





## ጌጣጌጦች






## በሀገራችን የሚገኙ የተለያዩ ባህላዊ የእንጨት ስራዎች






## ባህላዊ የቅርጫት እና ሠፌድ ስራ ውጤቶች






ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው ምስሎች በሀገራችን በተለያዩ ብሄረሰቦች ውስጥ የተሰሩ የዕይታ ጥበብ ውጤቶች ሲሆኑ እነዚህን ጥበባት ለመስራት የተለያዩ ተፈጥሯዊ ቁሶችን ተጠቅመዋል:: ከተጠቀሟቸው ቁሳቁሶች መካከል እንጨት፣ ሸክላ ፣ወርቅ፣ ብር ፣ ጥጥ የመሳሰሉት ይገኙበታል::

መልመጃ 1:- የተለያዩ ቀለማትን በመጠቀም በቤታችሁ የሚገኙ የባህል አልባሳት ጥልፍን በስዕል ሰርታቹ አሳዩ::

መልመጃ 2:- በሀገራችን ከሚገኙ ባህላዊ የእንጨት ወይም የሸክላ ስራዎች መካከል አንዱን በንድፍ ሰርታችሁ አሳዩ::

## 3.4.2 የዕይታ ጥበባት በማኅበረሰብ ውስጥ ከታሪክ አንፃር ያላቸው ሚና

ሀገራችን ኢትዮጵያ የብዙ ዘመናት ታሪክ እንዳላት ይታወቃል:: በዚህ የታሪክ ሂደት ውስጥ የተለያዩ የዕይታ ጥበብ ውጤቶች የሆኑ የቀለም ቅብ ስራዎች፣ ሐውልቶች፣ ቤተ-መንግስታት እንዲሁም ቤተ አምልኮዎች ተሰርተዋል:: ከእነዚህ ስራዎች መካከልም አብዛኞቹ በሀገራችን ታሪክ ውስጥ ትልቅ አሻራን አሳርፈዋል:: ታሪክን ከማስተላለፍ በተጨማሪ በዩኔስኮ የዓለም ቅርስነት በመመዝገብ ለሀገራችን የቱሪስት መስህብ በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ::

ታሪክን ለትውልድ ማስተላለፍ ያለው ዋና ጠቀሜታ አዲስ የሚመጣው ትውልድ የቀደምት አባቶቹን ዕውቀት፣ጥበብ እና ሥልጣኔ እንዲያውቅ እንዲሁም እንዲያስቅጥል ከተሰሩ ስህተቶች ደግሞ እንዲማር እና እንዳይደግም ነው:: ታሪክን ጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ በማስተላለፍ ውስጥ የዕይታ ጥበባት ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው:: ለምሳሌ የአክሱም ሐውልቶችን ብንመለከት ከ2000 ዓመታት በፊት የነበረውን የአክሱም ዘመነ መንግስት የሥልጣኔ ታሪክን አሁን ድረስ ጠብቀው አቆይተዋል::

ከዚህ በታች የምትመለከቷቸው ምስሎች ኢትዮጵያ በዩኔስኮ የዓለም ቅርስነት ያስመዘገበቻቸው ቅርሶች ናቸው::



የላሊበላ ውቅር ቤተክርስቲያን (ቤተ-ጊዮርጊስ)



የአክሱም ሐውልት





የጥያ ትክል ድንጋዮች





የሐረር ጀጎል ግንብ



የጎንደር ፋሲለደስ ቤተ-መንግስት

ሌላው በሀገር ታሪክ ውስጥ ትልቅ ስፍራን የሚይዘው ሠንደቅ ዓላማ ነው። ሠንደቅ ዓላማ የአንድን ሀገር ታሪክ፣ ህዝብ፣ ነፃነት እንዲሁም ባህል የሚወክል የዕይታ ጥበብ ውጤት ነው።

ሀገራችን ኢትዮጵያም ታሪኳን፣ ህዝቧን፣ ነፃነቷን የሚወክል ሠንደቅ ዓላማ አላት። ይህም ሠንደቅ ዓላማ ከታች እንደምትመለከቱት አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ቀለማት ከላይ ወደ ታች በአግድም ተደርድረው መሐሉ ላይ ክብ በሆነ ሠማያዊ መደብ ላይ በቢጫ መስመሮች የተዋቀረ ኮከብ እና የኮከቡ ጨረር ያለበት ነው። አሁን ባለው የኢትዮጵያ ሠንደቅ ዓላማ ላይ የሚገኘውን አርማ የሰራው “መስፍን ሃብተማሪያም” የተባለ ሰዓሊ ነው።

እነዚህ ቀለማት የሚወክሉት፡-

አረንጓዴ፦ የኢትዮጵያን ልምላሜ

ቢጫ፦ የኢትዮጵያን ተስፋ

ቀይ፦ ለኢትዮጵያ ነፃነት የተከፈለውን የደም መስዋትነት

አርማ፦ የብሄረሰቦችን እኩልነት፣ ትብብር፣ ተስፋ እና ዕድገት ነው።



መልመጃ 3፡- የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በቀለም ስላቹ አሳዩ።

## ማጠቃለያ

የኢትዮጵያን ሙዚቃ ከባህልና ታሪክ አንፃር ያለውን ግንኙነት በኑሮአችን ላይ ያለውንም ጥምረት ተመልክተናል፡፡ በህፃንነት እሽሩሩ በልጅነት ጨረቃ ድንቡል ቦቃ እንዲሁም ከሃይማኖት ስለ ያሬዳዊ ዝማሬ በጥቂቱ አይተናል፡፡ ወደፊት በጥልቀት የምንረዳቸው ሀሳቦች በመሆናቸው በደንብ መረዳት ይገባናል፡፡

ባህል ማለት የአንድን ማኅበረሰብ የአመጋገብ ፣ የአለባበስ ፣ የአምልኮ ስርዓት፣ የቤት አሰራርን የመሳሰሉትን በአንድ ላይ የሚይዝ ነው፡፡
የዕይታ ጥበባት ባህልን ለማሳደግ፣ ለማስተዋወቅ እና ለትውልድ ለማስተላለፍ ትልቅ ጥቅም አላቸው፡፡ አልባሳት፣ ጌጣጌጦች፣ የሸክላ ሥራዎች በአንድ ማህበረሰብ ባህል ውስጥ የሚገኙ የዕይታ ጥበባት ውጤቶች ናቸው፡፡ ታሪክን ከትውልድ ወደትውልድ ለማስተላለፍ የዕይታ ጥበባት ትልቅ ሚና አላቸው፡፡ የአንድ ህዝብ ታሪክ በሐውልት፣ በቀለምቅብ፣ በመፅሐፍት ሊተላለፍ ይችላል፡፡

## ማጠቃለያ ምዘና፡-

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ሐሰት በማለት መልሱ

   1. ሙዚቃ በአደዋ ጦርነት ላይ ምንም አስተዋፅኦ አልነበረውም፡፡-...........
   2. ሙዚቃ በማህበረሰብ ውስጥ መንፈሳዊ አገልግሎት በመስጠት ሰዎች ሃይማኖታዊ አምልኮዎችን የሚያከናውኑበት የጥበብ አይነት ነው፡፡..........
   3. ሕፃናት ለማስተኛት የሚያስችል ሙዚቃ አለ፡፡............
   4. አዝማሪዎች የሚጠቀሙበት የሙዚቃ መሳሪያ መሰንቆ ነው፡፡.................
   5. በአድዋ ጦርነት ጊዜ የአዝማሪዎች ሚና የአርበኞችን ስሜት በሙዚቃ ማነቃቃት ነበር፡፡...............
   6. ቅዱስ ያሬድ ኢትዮጵያዊ የሙዚቃ ሊቅ ነው፡፡.................
   7. ቅዱስ ያሬድ የደረሳቸው ዜማዎች ግዕዝ፣ ዕዝል ፣አራራይ ናቸው፡፡ ....................

8. የቅዱስ ያሬድ ዜማዎች ለአለማዊ አገልግሎት የሚውሉ ናቸው፡፡................
9. ሃዘንን በዜማ መግለፅ ይቻላል፡፡፡፡.................
10. ልጆች ተሰባስበው በዜማ መጫወት ይችላሉ፡፡............
11. የዕይታ ጥበባት ባህልን ለማሳደግ እና ለማስተዋወቅ ትልቅ ሚና አላቸው፡፡------------
12. የባህል አልባሳት ከዕይታ ጥበባት ውስጥ አይካተቱም፡፡---------
13. ጌጣጌጦች የዕይታ ጥበባት ውጤቶች ናቸው፡፡----------
14. የዕይታ ጥበባት ከታሪክ አንፃር ምንም ዓይነት ጠቀሜታ የላቸውም፡፡---------
15. የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በውስጡ ነጭ ቀለም ይገኛል፡፡-------

፪. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ፃፉ፡፡

1. የዕይታ ጥበባት ከባህል አንፃር ያላቸውን ጠቀሜታ በአጭሩ ግለጹ፡፡
2. የኢትዮጵያ ሠንደቅ ዓላማ በውስጡ የያዛቸውን ቀለማት ዘርዝሩ

# ምዕራፍ አራት

## ሥነ-ውበታዊ እሴት (ዋጋ)

### መግቢያ

ሙዚቃ የሰዎችን ስሜት ከመቆጣጠር አልፎ የአእምሮ ብቃትን ለማሳደግ ከፍ ያለ አስተዋፅኦ እንዳለው በርካታ ጥናቶች አረጋግጠዋል፡፡ ሙዚቃ ከሰው ልጅ ስሜት ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ስላለው የሰዎችን አእምሮ በማዝናናት በውስጣቸው የሚመላለሱትን ስሜቶች እንዲገልፁ ከማድረግ በተጨማሪ የተማሪዎችን ስሜት በማነቃቃት ለትምህርት ዝግጁ እንዲሆኑ ያግዛል ፡፡

በዚህም ምክንያት ሰዎች በየትም ቦታና አጋጣሚ ራሳቸውን የመግለፅ ብቃት ይኖራቸዋል፡፡ ሙዚቃ አንዱና ዋነኛ የጥበብ አካል በመሆንዋ ሙዚቃ ከመጫወት የምናገኘው ጥቅም  የተለያዩ ክህሎቶችን ማዳበር ነው፡፡

ክህሎት የሚዳብረው የአካል ቅልጥፍናን እና የአእምሮ ብቃትን በማዋሃድ ነው፡፡ ሙዚቃ መጫወት እነዚህን የአእምሮ ብቃትንና የሰውነት ክፍሎችን በማጣመር ተማሪዎች የፈጠራ ብቃታቸው እንዲያድግ ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

ኪነ-ጥበብ ማህበረሰብን በሰለጠነ መንገድ ለመገንባትና የፈጠራ ክህሎት ያለው ትውልድ እንዲፈጠር የሚያደርገው አስተዋፅኦ ጉልህ ነው፡፡ ስለዚህ ኪነጥበብን መረዳት እና ማወቅ ያለው ጠቀሜታ በሶስት መንገድ ከፍለን ማየት

እንችላለን፡፡  የማህበራዊ ኑሮን ልምድ ለመገንባት፣ አካልን ለማዳበርና የአዕምሮን ዕውቀት ለማዳበር ይጠቅማል፡፡

የዕይታ ጥበባትን መስራት እና መለማመድ አንድ ሰው በሕይወቱ ውስጥ የሚያጋጥሙትን ጥሩም ሆነ መጥፎ አጋጣሚዎችን ፈጠራ በተሞላበት እና በራሱ መንገድ እንዲጋፈጥ እና እንዲወጣ አቅምን እና ችሎታን ይሰጠዋል። የዕይታ ጥበባት በባህሪያቸው አካባቢን በጥልቀት ማስተዋልን እንዲሁም በማስተዋልን ማሰብን ይጠይቃሉ። ይህም አንድን የዕይታ ጥበብ ለመስራት በምንለማመድበት ወቅት አካባብያችንን አንድንቃኝ ፣ ተፈጥሮን እንድናስተውል፣ እንድንመረምር እና የራሳችንን ፈጠራ እንድናዳብር እድሉን ይሰጠናል።

## ዝርዝር የመማር ውጤት፡-

ይህንን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ ፡-

- ሙዚቃን መለማመድ ያለውን ጠቀሜታ ትረዳላችሁ።
- ሥነ-ውበታዊ እሴቶችን ታደንቃላችሁ።
- የቴአትር ጠቀሜታን ትረዳላችሁ።
- በሚና ጨዋታ ትጫወታላችሁ።
- ስለ አገር በቀል የቴአትር ጥበብ ታውቃላችሁ።
- የዕይታ ጥበባትን መለማመድ ያለውን ጠቀሜታ ትረዳላችሁ።
- አገር በቀል የቤትና የጌጣጌጥ አሰራሮችን አውቃቸሁ ታደንቃላችሁ።
- የዕይታ ጥበባት ዘርፎችን ታውቃላችሁ።

## 4.1 ሙዚቃን መለማመድ ያለው ጠቀሜታ (ዋጋ)

ሙዚቃ ስሜትን የምንገልጽበት አንዱ የጥበብ ክፍል ሲሆን አንድ ሙዚቃ በምንጫወትበት ጊዜ የውሰጥ ስሜታችንን ደስታ፤ ሐዘን ወይንም ማንኛውንም አይነት ስሜት ሙዚቃዊ ድምፃችን በመጠቀም የምንገልፅበት የጥበብ መንገድ ነው፡፡ ስሜታችንን በሙዚቃ የመግለፅ ልምምድ ትልቁ ጥቅም እራሳችንንም ሆነየተማርነውን ትምህርት በአግባቡ መግለፅ እንድንችል እና በራስ መተማመንእንዲኖረን ይረዳናል፡፡

ሙዚቃ በዋናነት ዜማ፤ ሰልተ ምት ፣ ቅንብር እና ግጥም አሉት ፡፡ ማንኛውንም አይነት ትምህርት በሙዚቃ አጋዥነት ብንማር የተማርናቸውን ትምህርቶች ለረጅም ጊዜ ማስታወስ እንችላለን ይህም ማለት የሙዚቃ ልምምድ የአእምሮን የማስታወስ ችሎታን ከፍ እንዲል ያደርጋል ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሙዚቃ የአእምሮ የማሰብ ብቃትን ስለሚያዳብር በተማሪዎች ላይ የፈጠራ ችሎታን ለማሳደግ ከፍ ያለ አስተዋፅኦ በረክታል፡፡



ምስል 1፡- ሙዚቃ ለአእምሮ መዳበር እንደሚያስፈልግ የሚያሳይ

- ግጥም የመዝሙር(የዘፈን) አንዱ ክፍል ነው፡፡ በመሆኑም ግጥም እና ዜማን በድምፅ በመለማመድ አራቱን የቋንቋ ክህሎቶች እንድናዳብር ያግዛል፡ ፡ እነዚህም መሰረታዊ ክህሎቶች መስማት፤መናገር፤ማንበብ እና መፃፍ ናቸው፡፡

ሙዚቃ የማህበረሰቡ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ታሪካዊ፣ ሀገራዊ እና መንፈሳዊ ክንዋኔዎችን መግለጫ እንደመሆኑ የአካባቢያችንን ባህላዊ ክንዋኔዎች በመዝሙር እንድንገልፅ ያደርጋል፡፡ ሙዚቃ የአንድን ማህበረሰብ ያለፈውን ታሪክ እንደ መስታወት የሚያሳይ በመሆኑ ሙዚቃን በመለማመድ ውስጥ የማህበረሰቡን ያለፈውን ታሪክ ምን ይመስል እንደነበረ ያስረዳናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሀገራዊ ይዘት ያላቸውን ሙዚቃዎች በመለማመድ ስለ ሀገራችን ጠለቅ ያለ እውቀት እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ የቴዎድሮስ ካሳሁን ጥቁር ሰው፣ የእጅጋየሁ ሽባባው አድዋ የሚባሉት ዘፈኖች ተጠቃሽ ናቸው፡፡




ምስል 2፡- የአድዋ ጦርነትን የሚያሳይ ምስል

**መልመጃ 1፡-** የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዶቦታዎችን በመሙላት መልሱ

1. ሙዚቃ በዋናነት ምን ምን ይይዛል?
   ሀ.ዜማ(ድምፅ)　　ሐ.ግጥም
   ለ. ስልተ ምት(ሪትም)　　መ. ሁሉም መልስ ይሆናል

2. ሙዚቃን መለማመድ የሚያስገኘው ጥቅም ምንድን ነው?
   ሀ. የፈጠራ ችሎታን ያዳብራል　　ሐ.ራስን ለመግለፅ ያግዛል
   ለ. የቋንቋን ችሎታን ያሳድጋል　　መ.ሁሉም
3. ሙዚቃን መለማመድ ስንት አይነት የቋንቋ ክህሎቶችን ያዳብራል?
   ሀ. አንድ　　ሐ.ሦስት
   ለ. ሁለት　　መ. አራት

### 4.1.1 ሀገር በቀል ሙዚቃዎችን ማወቅና ማድነቅ

**4. ዝርዝር የመማር ውጤት**

ይህንን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ ፡-

- የአገር በቀል ሙዚቃዎችን ታደንቃላችሁ፡፡
- የአገር በቀል የሙዚቃ መሣሪያዎችን ታውቃላችሁ፡፡
- አራቱን ዋና ዋና የኢትዮጵያን ቅኝቶች ታውቃላችሁ፡፡

ሀገር በቀል ሙዚቃዎች የሚባሉት ማህበረሰቡ በሚያደርገው የእለት ከእለት ግንኙነት የተፈጠሩ ሆነው ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ የመጡ እና ማህበረሰቡ ለአስፈላጊ ተግባር የሚጠቀምባቸው ሙዚቃዎች ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ሙዚቃ ከሚያስብሉት መለያዎች ውስጥ ሁለት ነገሮችን ያካትታል፡፡ የመጀመሪያው የባህላዊ የሙዚቃ መሳሪዎች ሲሆኑ ሁለተኛው ደግሞ የምንጠቀምባቸው ቅኝቶች ናቸው፡፡

### 4.1.2 የኢትዮጵያ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች

በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች በርካታ የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያዎች አሉ፡፡ የሙዚቃ መሳሪያዎች በሦስት መመደብ ይቻላል፡፡እነሱም በትንፋሽ፣ በምት እና በክር ይባላሉ፡፡

### 4.1.3 በትንፋሽ ድምፅ ከሚፈጥሩ መሳሪያዎች መካከል:-

ዋሽንት:- ዋሽንት በትንፋሽ ድምፅ የሚፈጥር ሃገር በቀል የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡

- ከሸንበቆ፣ ከፕላስቲክ ትቦ (ኮንዲት) ሊሰራ ይችላል፡፡
- አራትና ከዛም በላ የተመጠነ ድምፅ እንዲፈጥሩ ተደርገው የሚበሱ ቀዳዳዎች አሉት፡፡
- ቀላልና ለመያዝ አመቺ የሆነ የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡



ምስል 3:- ዋሽንት

### 4.1.4 በምት (ግጭት) ድምፅ የሚፈጥሩ መሳሪያዎች:-

እነዚህ የሙዚቃ መሳሪያዎች ከቆዳና መሰል ነገሮች ይሰራሉ፡፡

- የተለያዩ የከበሮ አይነቶችን ለተለያዩ ግልጋሎቶች እንጠቀምባቸዋለን፡፡
- በመምታት ድምፅ ይፈጥራሉ፡፡




ምስል 4፡- የተለያዩ የከበሮ አይነቶች

- በእጅ ወይም መምቻ ዱላ በመጠቀም እንጫወታለን፡፡

### 4.1.5 የክር (በንዝረት) ድምፅ የሚፈጥሩ መሳሪያዎች

- ክራር ፤በገና እና መሰንቆ ወ.ዘ.ተ መጥቀስ እንችለለን፡፡
- ክራር ቋሚ እንጨት፣ ሁለት አግድም እንጨቶች፣ ድምፅን ለማጉላት የድምፅ ሳጥንና ክሮቹን ከፍ አድርጎ ለመያዝ የሚያገለግል ብርኩማ የሚባል መወጠሪያ እንጨት አለው፡፡
- ተጨማሪም መቃኛና አምስት ወይም ከዚያ በላይ ክሮች ይኖሩታል፡፡
- ለመንፈሳዊና ለዓለማዊ ሙዚቃ ያገለግላል፡፡



ምስል 5፡- የክራር ምስል

ማሲንቆ (መሰንቆ)፡- የክር የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን ለሃይማኖታዊና ለዓለማዊ ሙዚቃ ማጀቢያነት ያገለግላል። ቋሚ እንጨት፣ የድምፅ ሳጥን፣ መወጠሪያ፣ መገዝገዣ (መምቻ) ደጋን (ቅንፍ) እንጨት አሉት።



ምስል 6፡-የመሰንቆ ምስል

በገና፡- ቀደምት የሙዚቃ መሳሪያ ነው።

- ለመንፈሳዊ ግልጋሎት ብቻ ይውላል።
- አስር ክሮች አሉት።



ምስል 9፡- የበገና ምስል

### 4.1.6 አራቱ የኢትዮጵያ ባህላዊ ቅኝቶች

በሀገራችን ሙዚቃ ውስጥ በአብዛኛው የምንጠቀማቸው የሙዚቃ ቅኝቶች በአምስት ድመፆችን ላይ የተመሰረቱ ናቸው። አምስት የተለያዩ የሙዚቃ ድመፆችን የያዘ የሙዚቃ ቅኝት ወይም ስኬል (ፔንታቶኒክ ስኬል) ይባላል፡፡ በዋናነት በኢትዮጵያ ውስጥ ከምንጠቀምባቸው ቅኝቶች ውሰጥ ታዋቂዎቹን ብቻ ብንጠቀስ ትዝታ፣ ባቲ፣ አምባሰል እና አንቺ ሆዬ የሚባሉትን እንደመነሻ ማወቅ ጥሩ ነው። በእነዚህ አራት ቅኝቶች የተሰሩ ትዝታ፤ባቲ፤ አምባሰል እና አንቺ ሆዬ የሚባሉ ዘፈኖች አሉዋቸው።

ቅኝቶቹን በአግባቡ ለመረዳት በእያንዳንዱ ቅኝቶች የተሰሩትን ሙዚቃዎች በትምህርት ቤት እንዲሁም በቤታችን፤ በተለያዩ ሬዲዮና ቴሌቪዥን አማካኝነት የምንሰማውን ሙዚቃ በመስማት የእያንዳንዱ ቅኝቶች ቃና መለየትና ማድነቅ ይቻላል።

**ትዝታ :-** በርከት ያሉ ድምፃዊያን ትዝታ ዘፈንን ያዜሙ ቢሆንም በድምፃዊ መሀሙድ አህመድ የተዜመው የትዝታ ዘፈንን ደጋግሞ ማዳመጥ ስለ ትዝታ ቅኝት መረዳት ይቻላል።

**ባቲ:-** በርከት ያሉ ድምፃዊያን ባቲ ዘፈንን ያዜሙ ቢሆንም በድምፃዊ ባህሩ ቃኜ የተዜመውን ባቲ ዘፈን ደጋግሞ ማዳመጥ ስለ ባቲ ቅኝት መረዳት ይቻላል።

**አምባሰል :-** በርከት ያሉ ድምፃዊያን አምባሰል ዜማን አዜመዋል። በድምፃዊት ማሪቱ ለገሰ የተዜመው የአምባሰል ዘፈንን ደጋግሞ ማዳመጥ ስለ አምባሰል ቅኝት መረዳት ይቻላል።

**አንቺ ሆዬ:-** ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ አብዛኛው የሰርግ ዘፈኖች በአንቺ ሆዬ ቅኝት የተሰሩ በመሆናቸው የተወሰኑትን የሰርግ ዘፈኖች ደጋግሞ መስማት ስለ ቅኝቱ እንድንረዳ ያስችላል።

### 4.1.7 የምንሰማባቸው መንገዶች

የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃ መስማትና ማየት በቻልንበት አጋጣሚ ሁሉ በአንክሮ ማድመጥና ምን ምን የሙዚቃ መሳሪዎች እንዳሉበት መመርመር ያስፈልጋል።

ሙዚቃ ልናዳምጥ የምንችልበትን ሁኔታ ከቤተሰቦቻችን ጋር በመነጋገር ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ትላልቅ ሰዎችን ስለምንሰማው ሙዚቃ በመጠየቅ ያለንን ግንዛቤ መጨመርና ማዳበር ጥሩ ነው፡፡

መልመጃ 2፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ

1. ሀገር በቀል ሙዚቃ የሚባለው የቱ ነው?
   ሀ. ባህላዊ ሙዚቃ                ሐ. አፍሪቃ ሙዚቃ
   ለ .ዘመናዊ ሙዚቃ                መ. መልሱ አንተሰጠም
2. ከሚከተሉት ውስጥ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ የቱ ነው?
   ሀ. ክራር                ሐ. ዋሽንት
   ለ. መሰንቆ                መ. በገና
3. ከሚከተሉት ውስጥ የምት የሙዚቃ መሳሪያ የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ክራር                ሐ. ከበሮ
   ለ. መሰንቆ                መ. በገና
4. ከሚከተሉት ውስጥ በንዝረት ድምፅ የሚያወጣው የሙዚቃ መሳሪያ የቱ ነው?
   ሀ. ክራር                ሐ. መሰንቆ
   ለ. በገና                መ. ሁሉም
5. ፔንታቶኒክ ስኬል ባለ ስንት ድምፅ የሙዚቃ ቅኝት ነው?
   ሀ. ባለ ሰባት                ሐ. ባለ አስራ ሀለት
   ለ. ባለ አምስት                መ. መልሱ አልተሰጠም
6. ከሚከተሉት ውስጥ የሙዚቃ ቅኝት ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ትዝታ                ሐ. መሰንቆ
   ለ. አምባሰል                መ. ባቲ
7. ከሚከተሉት ውስጥ የሀገር በቀል የሙዚቃ መሳሪያ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. እምቢልታ                ሐ. ክራር

ለ. ጊታር                መ. ከበሮ

## 4.2 የውዝዋዜ ጥበብን መለማመድ ያለው ጠቀሜታ

ክዋኔ ጥበባት ተብለው ከሚመደቡት መካከል ውዝዋዜ አንዱ ነው፡፡ ውዝዋዜ የሰውነት አካል እንቅስቃሴን በመጠቀም የሚደረግ የክዋኔ ጥበብ ነው፡ ፡ በዚህም ሰዎች ታሪካቸውን፡ ባህላቸውን፡ ስሜታቸውን እና ልዩ ልዩ ድርጊታቸውን በውዝዋዜ አማካኝነት ይገልጹበታል፡፡

ዝርዝር አጥጋቢ የመማር ውጤት

- በሚና ጨዋታ፡ ውዝዋዜ ትጨፍራላችሁ፡፡
- ስለ ክዋኔ ጥበባት ሚና ትረዳላችሁ፡፡

ውዝዋዜ የሰውነት አካልን በማንቀሳቀስ፡ ቅልጥፍናን ለመጎናፀፍ እና ጤናማ የሆነ ክብደት እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ሰውነታችን ቀልጣፋ ሲሆን በተዘዋዋሪ መንገድ አዕምሮን ፈጣን እና ንቁ ስለሚሆን ለሌሎች ትምህርቶች ተማሪዎች የሚኖራችሁን አቀባበል ያሳድጋል፡፡ ውዝዋዜ በተለያየ መንገድ ልንመለከተው እንችላለን፡፡ የማህበራዊ ኑሮን ልምድ ለመገንባት፣ አካልን ለማዳበርና የአዕምሮን ዕውቀት ለማዳበር ይጠቅማል፡፡

የማህበራዊ ኑሮን ልምድ ለመገንባት፡- የመንፈስ ጭንቀትን ለማስወገድ ይጠቅማል፡ ከትምህርት ክፍለ ጊዜ መጀመሪያ ላይ ልጆች በውዝዋዜ እንዲጫወቱ፡ እንዲዝናኑ ማድረግ፡፡ የተዘጋጀ ውዝዋዜ አይነት የብሔር ብሔረሰብ ውዝዋዜ ቢሆን አሳታፊ ልጆች አቀራራቢ ስለሚሆን የቡድን ስሜትና ህብረት ለማስገኘትይጠቅማል፡፡ በሚጫወቱት የተለያዩ ኪነ-ጥበባዊ ጨዋታዎች እራሳቸውን ችለው እንዲጫወቱ ማድረግ ኃላፊነት መውሰድ እንዲያውቁ ይጠቅማል፡፡

አካልን ለማዳበር ይጠቅማል፡- የተለያዩ ኪነ-ጥበባዊ ዕንቅስቃሴ ከሚጠይቁ ድርጊቶች መካከል ውዝዋዜ አንዱ ነው፡፡ ውዝዋዜ አካላችንን ቀልጣፋና የተስተካከለ አቋም እንዲኖረን ያስችላል፡፡ በዚህም ጤናማ ደስተኛ እንድነሆን ያደርጋል፡፡

አዕምሮን በእውቀት ለማዳበር፡- የአገርን ባህልን ታሪክ ለማወቅ ይጠቅማል፡፡ በአገራችን ኢትዮጵያ ከሰማንያ በላይ ብሔረሰብ እንዳለ ይታወቃል እነዚህም ህዝቦች ታሪካቸውን ባህላቸውን ከሚገልጹበት መንገዶች መካከል ውዝዋዜ አንዱ ነው፡፡ ስለዚህ ስለብሔረሰቦች ውዝዋዜ በምናጠናበት ወቅት የእውቀት አድማሳችሁም በዛው ልክ ያድጋል ይሰፋል ማለት ነው፡፡

## 4.3 የትያትር ጥበብን መለማመድ ያለው ጠቀሜታ

**የትምህርቱ ዝርዝር አላማ፡-**

ይህንን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ሥነ-ውበታዊ እሴቶችን ታደንቃላችሁ፡፡
- የቴአትር ጠቀሜታን ትረዳላችሁ፡፡
- በሚና ጨዋታ ትጫወታላችሁ፡፡

ኪነ ጥበብ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚያመጣውን ጠቀሜታ በሶስት መንገድ ከፍለን ማየት እንችላለን፡፡ በመህበራዊ፡ አካላዊና አዕምሮአዊ በማለት ዘርዝረን እንመልከታቸው፡፡

### 4.2.1 የማህበራዊ ኑሮን ልምድ ለመገንባት

የመንፈስ ጭንቀትን ለማስወገድ ይጠቅማል፡ ከትምህርት ክፍለ ጊዜ መጀመሪያ ላይ ልጆቹ እንዲጫወቱ በመዚቃ፡ በዳንስ፡ ትያትርና ስዕል እንዲዝናኑ ማድረግ፡ ፡ የተዘጋጀውም የጨዋታ አይነት አሳታፊ ልጆች አቀራራቢ መሆን አለበት ይህም የበድን ስሜትና ህብረት ለማስገኘት ይጠቅማል፡፡ ያለ መምህሩ እርዳታ እራሳቸውን ችለው እንዲጫወቱ ማድረግ እራስን በስነ ስርዓት ለማነፅ ይጠቅማል፡ ፡ ልጆች ያላቸውን ዝንባሌ ወይም የተሰጣቸውን መክሊት ለማወቅ ይጠቅማል፡፡ በሚጫወቱት የተለያዩ ኪነ-ጥበባዊ ጨዋታዎች እራሳቸውን ችለው እንዲጫወቱ ማድረግ ኃላፊነት መውሰድ እንዲያውቁ ይጠቅማል፡፡

### 4.2.2 አካልን ለማዳበር ይጠቅማል

የተለያዩ ኪነ-ጥበባዊ ዕንቅስቃሴን የሚጠይቁ ድርጊቶች መዝናናት፡ ማሰብና ማስተዋል የሚጠይቁ ጨዋታዎች እና ቅልጥፍናንና ሰውነት እንደ ልብ ለማዘዝ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ለምሳሌ፦ ውዝዋዜ፡ የሰውነት አካልን እንደ ልብ ለማንቀሳቀስ ቅ ልጥፍናን ለመጎናፀፍ እና ጤናማ የሆነ ክብደት እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ ማሰብናማስተዋል የታከለባቸው የዝላይ፡ የመሮጥ፡ የመቀመጥና ቁጭ ማለትን የሚጠይቁጨዋታዎችም አስተዋይና ሸንቃጣ የሰውነት አቋም እንዲኖራችሁ ያደርጋል፡፡

### 4.2.3 አዕምሮን በእውቀት ለማዳበር

የአገርን ታሪክ ማወቅ አዕምሮን በእውቀት ለማበልፀግና የአገር ፍቅር እንዲኖራችሁ ያደርጋል፡፡ በአገራችን ኢትዮጵያ በተለያየ የሙያ ስራ መስክ ተሰማርተው ስኬታማ የሆኑ ግለሰቦች ታሪክ ማወቅ መነሳሳት እንዲኖራችሁና የስራ መስካችሁንም በልጅነት እድሜያችሁ እንድታውቁ ያድርጋችኃል፡፡ ስለ አገር እና አርአያ የሆኑ ግለሰቦች ታሪክን ማወቅ የእውቀት አድማሳችሁ እንዲሰፋ እና የህይወት ግብ እንዲኖራችሁ ያደርጋል፡፡

ከዚህ በመቀጠል ልዩ ልዩ ጨዋታዎችን እንመልከት፡- ይህ ጨዋታ ልጆችን ያቀራርባል፡ ፈጣሪና እራስን ለመቆጣጠር እንዲሁም ለማዝናናት ይጠቅማል፡፡

## 4.3 አገር በቀል ጨዋታዎች

### አስቀኝ

ከ አስር እስከ አስራአምስት ሆናችሁ ክብ ስርታችሁ መቆም፡ ከአንድ ጀምሮ መጨረሻ እስካለው ልጅ ቁጥር መቁጠር የተሰጠውን ቁጥር መለያው ስለሆነ እያንዳንዱ ተማሪ ቁጥሩን መያዝ፡ በመቀጠል መምህሩ ጀምር ብሎ አንድ ቁጥር ሲጠራ የተጠራው አንድ ተማሪ ወደ ክቡ መኃል በመግባት የተለያዩ ድራማዊ እንቅስቃሴዎችን ያለ ንግግር በማድረግ ለማሳቅ መሞከር የሳቀ ወይም የተናገረ ከጨዋታው ይወጣል፡፡ በዚህ ሂደት መጨረሻ የቀረው ልጅ አሸናፊ ይሆናል ማለት ነው፡፡

የጨዋታው ሕግ፡- በዚህ ጨዋታ ድምጽ ማውጣት እና መናገር አይፈቀድም፡፡ እንቅስቃሴውን የምታሳዩት ድምጽ አልባ እንቅስቃሴን በማድረግ ይሆናል፡፡

### መልመጃ

-ቀጥሎ የቀረበውን ባልና ሚስት የተሰኘ ታሪክ አንብባችሁ በድርጊት ብቻ ሶስት በመሆን ማለትም ባል፡ ሚስት እና ተማሪው በመሆን በድምጽ አልባ ድራማ መልክ በመለማመድ በጓደኞቻችሁና በመምህራችሁ ፊት አቅርቡ፡፡

### 4.3.1 ሞኝ ባልና ሚስት

በድሮ ጊዜ ሁለት ሞኝ ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ዶሮ አረዱና ሚስተየዋ ሠርታ ሊበሉ ሲሉ ለጥርሳቸው መጎርጎሪያ የሚሆን ሳር የሌለ መሆኑን ያስታውሱና ሊያመጡ ወደ ዱር ሄዱ፡፡ ወደ ዱር ሲሄዱ መንገድ ላይ አንድ ተማሪ አገኛቸው፡፡ ተማሪውም፡-

ወዴት ትሄዳላችሁ? ሲል ጠየቃቸው፡፡

ዶሮ አርደን ሰርተን አስቀምጠን ለጥርሳችን መጎርጎሪያ ሳር ልናጭድ ነው፡

ቤታችሁ የት ነው?

ያ እዛ ማዶ እመንገዱ ዳር ያለው ነው ብለው ነግረውት ወደ ሳር አጨዳ

ተጓዙ። ተሜም እቤታቸው ሄደና ዶሮ ወጣቸውን ግጥም አድርጎ በልቶ ጠፋ። ባልና ሚስት ሣራቸውን አጭደው ተሸክመው እቤት ደረሱና ቢያዩ የወጡ ድስት ባዶውን ሆኖ ዝንብ ወሮታል። በዚህ ጊዜ ዶሮ ወጣቸውን ዝንብ ነው የበላው ብለው በማመን በቤቱ ውስጥ ውር ውር የሚለውን ዝንብ መግደል ጀመሩ። ዝንቦች በእንስራው፣ በምጣዱ፣ በማሰሮ ላይ ሲያርፉ እነሱን አገኛለሁ በማለት የቤቱን ዕቃ ሁሉ ሲያነክቱ ቆዩ። በመጨረሻም አንዲት ዝንብ እሴትየዋ ግንባር ላይ አረፈች። በዚህ ጊዜ ሴትየዋ ዝንቧ ተነስታ እንዳትበር ቀስ ብላ በምልክት ባሏን ጠቆመችው። ሰውየውም በያዘው ቆመጥ አስተካክሎ ግንባሯን ሲላት ጊዜ ውሃ ሳትል አረፈች።

### 4.4 የዕይታ ጥበብን መለማመድ ያለው ጠቀሜታ

**ዝርዝር የመማር ውጤት**

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የዕይታ ጥበባትን መለማመድ ያለውን ጠቀሜታ ትረዳላችሁ።
- አገር በቀል የቤትና የጌጣጌጥ አሰራሮችን ታውቃላቹ እንዲሁም ታደንቃላችሁ።
- በምትኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ የምታይዋቸውን ብዝሃ ባህሎች እና ስርዓቶች ማድነቅ ትችላላችሁ።
- የዕይታ ጥበባት ዘርፎችን ታውቃላችሁ።
- በአካባቢያችሁ እና በዙሪያቹ ያሉትን ነገሮች በአስተውሎት መመልከትና መረዳት ትችላላችሁ።
- በአካባቢያቹ ያስተዋላችሁትን ነገር በዕይታ ጥበብ መግለፅ ትችላላችሁ።

የዕይታ ጥበባትን መለማመድ (መስራት) ያለውን ጠቀሜታ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች መመልከት እንችላለን እነሱም፦ ከስነ-ውበት አንፃር፣ ስሜትን ከመግለፅ አንፃር፣ ከአዕምሮ እድገት አንፃር እንዲሁም ከማህበራዊ ግንዛቤ አንፃር ናቸው።

4.4.1 ከስነ-ውበት አንፃር፦ የዕይታ ጥበባትን መስራት ከስነ-ዉበት አስተሳሰብ ወይም ትርጉም ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው። አንድን የሥነ-ጥበብ ስራ በምንሰራበት ወቅት ለስነ-ውበት እሳቤ ሰፊ ተጋላጭነት ይኖረናል። በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ስንኖር በዚያ ማህበረሰብ ባህል ውስጥ ያለውን የስነ-ውበት ሀሳብ እና አመለካከት እንድንገነዘብ እና እንድናደንቅ ይረዳናል።

4.4.2 ስሜትን ከመግለፅ አንፃር፦ የዕይታ ጥበባትን መስራት ስለ አንድ አካባቢ፣ ማህበረሰብ ወይም ሁኔታ የተሰማንን ስሜት በቀለም፣ በቅርፅ፣ በመስመር በመሳሰሉት እንድንገልፅ እድልን ይሰጠናል። ይህም ስለ አንድ ነገር የተሰማንን ስሜት ለመግለጽ ወላጆቻችን ወይም ከእኛ ውጪ ሌላ ሰው ላይ ጥገኛ እንዳንሆን ያደርገናል። በተጨማሪም ሀላፊነት በተሞላበት መልኩ የራሳችንን ሀሳብ እንዲሁም ስሜት ለሌሎችህ እናጋራበታለን።

4.4.3 ከስነ-አዕምሮ አንፃር፦ የዕይታ ጥበባትን መስራት እና መለማመድ ለአንድ ሰው የአዕምሮ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው። ይህም የዕይታ ጥበባትን በምንሰራበት ወቅት በሚያጋጥሙን ልዩ ልዩ አጋጣሚዎች አዕምሯችን የተለያዩ ዓይነት ስሜቶችን እንዲለማመድ እና እንዲያውቅ ብሎም ችግር በሚያጋጥመን ወቅት ደግሞ ቀላል በሆነ እና ጥበብ በተሞላበት መንገድ እንድንፈታ ይጠቅመናል።

4.4.4 ከማህበረሰብ አንፃር፦ የተለያየ ልማድ ካላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር ተባብሮ መስራት ለማህበረሰባዊ እድገት እጅግ ጠቃሚ ነው። ለምሳሌ የመማሪያ ክፍል ውስጥ የተለያየ ጠባይ፣ ባህሪ፣ የኑሮ ሁኔታ፣ የትምህርት አቀባበል ያለቸው ተማሪዎች ይገኛሉ። ከእነዚህ ተማሪዎች ጋር በጋራ መስራት፣ የተለያዩ የትምህርት መርጃ ቁሳ ቁሶችን መዋዋስ እንዲሁም ችግሮችን መፍታት የመሳሰሉትን በምሰራበት ወቅት የዕይታ ጥበብ ትምህርት እነዚህ የተለያየ ጠባይ ካላቸው ተማሪዎች ጋር በጋራ እንድንሰራ ይረዳናል። ይህም በማህበረሰባችን ውስጥ ያሉትን ብዝሃ ባህሎች እንዲሁም ስርዓቶች እንድናደንቅ እና እንድናከብር ያስችለናል።

መልመጃ 1

1. የዕይታ ጥበባት ከስነ-ውበት አንፃር ያላቸውን ጠቀሜታ ፃፉ፡፡
2. የዕይታ ጥበባት ከስነ-አዕምሮ አንፃር ያላቸውን ጠቀሜታ ፃፉ፡፡

መልመጃ 2፡- ተማሪዎች ከምታደንቋቸው ባህላዊ የዕይታ ጥበባት ውጤቶች ቢያንስ ሦስቱን በስዕል ሰርታችሁ አሳዩ፡፡

### 4.4.5 አገር በቀል የቤት አሰራሮችን፣ ጌጣጌጦችን ማወቅ እና ማድነቅ

ይህን ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ፡-

- አገር በቀል የቤት አሰራሮችን ማድነቅ ትችላላችሁ፡፡
- የሀገራችንን የተለያዩ ጌጣጌጦች ታውቃላችሁ እንዲሁም ታደንቃላችሁ፡፡

ሀገር በቀል ዕውቀት ማለት የአንድ ሀገር ማህበረሰቦች ከምስረታቸው ጀምሮ በዕለት ከዕለት ሕይወታቸው ውስጥ እያሻሻሉ እና እያዳበሩ የሚመጡት የራሳቸው የሆነ የአኗኗር ባህል ወይም ስልት ነው፡፡ በሀገራችን ብዙ ብሄረሰቦች እንደመኖራቸው መጠን እነዚህ ብሄረሰቦች የራሳቸው የሆነ ባህል እና ትውፊት አላቸው፡፡ እነዚህ ማህበረሰቦች ሀገር በቀል ዕውቀቶችን በተለያዩ የዕለት ከዕለት የአኗኗር ስርዓታቸው ውስጥ በስፋት ሲተገብሯቸው እናያለን፡፡ ከእነዚህ ሀገር በቀል ዕውቀቶች መካከል የዕይታ ጥበባት ውጤቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህ የዕይታ ጥበባት የቤት አሰራሮች፣ ጌጣጌጦች፣ የአለባበስ ስርዓቶች፣ ስዕላት፣ የመገልገያ ቁሳቁሶች እና የመሳሰሉትናቸው፡፡ በዚህ ንዑስ ምዕራፍም የተለያዩ አገር በቀል የቤት አሰራሮችን፣ ጌጣጌጦችን፣ የመገልገያ ቁሳቁሶችን እናያለን እንዲሁም እናደንቃለን፡፡

የዕይታ ጥበባትን ማድነቅ የሚወሰነው የዕይታ ጥበባት ከማህበረሰቡ ታሪክ ካላቸው ጠቀሜታ አንፃር እንዲሁም ይዘታቸውን በማወቅ ነው። የዕይታ ጥበብን ባህላዊ ይዘት ፣ የተሰሩበትን ቁሶች እና ጠቀሜታ እንዲሁም ስነ ውበታዊ ሀሳብ ሳይረዱ ማድነቅ ሆነ ማወቅ አስቸጋሪ ነው።

የዕይታ ጥበባት ውጤቶች የኋላ ታሪክን እንዲሁም የተሰሩበትን ቦታ እንዲሁም መነሻ እንድናውቅ ይረዱናል። በተጨማሪ ደግሞ በወቅቱ የነበረውን ማህበረሰብ ስነ ውበታዊ አረዳድ እና አገላለፅ እንድናውቅ ያደርጋል።በሀገራችን የሚገኙ የተለያዩ የቤት አሰራሮች የዕይታ ጥበባት ውጤቶች ናቸው። እንዲሁም የተለያዩ ጌጣጌጦች የየራሳቸው ባህላዊ ትርጓሜ፣ ጠቀሜታ እንዲሁም የአደራረግ ስርዓት አላቸው። በሃገራችን ያሉት ቤቶች የሚሰሩበት መንገድ የሚገኙበትን አካባቢ የአየር ጠባይ ያማከለ ሲሆን የሚሰሩባቸው ቁሶችም በአካባቢው የሚገኙ ናቸው። እነዚህን ቤቶች የማስጌጫ እና የማሳመሪያ መንገዶች ሲኖሩ ከሚያስጌጡባቸው መካከል የተለያዩ ቀለማት ያላቸው የአፈር አይነቶች በመበጥበጥ የተለያዩ ቅርፆችን እና የመስመር ዓይነቶችን በመጠቀም ግድግዳዎቻቸውን ማስዋብ የተለመደ ነው። እነዚህ በቤቶቻቸው ግድግዳዎች ላይ ስዕሎችን ለመስራት የሚጠቀሙባቸው ቀለማት በአካባቢያቸው ከሚገኙት ቀለማት ጋር ተናባቢ ናቸው። ከታች ባሉት ምስሎች በሃገራችን የሚታወቁ ዋና ዋና የቤት አሰራሮችን እና የሚያስጌጡባቸውን መንገዶች እንመለከታለን።









ቀጥሎ የቀረቡት ምስሎች ደግሞ በሀገራችን የሚገኙትን ልዩ ልዩ ጌጣጌጦችን ዓይነቶቻቸውን ያሳዩናል፡፡







መልመጃ 3፡- በሀገራችን ካሉ ባህላዊ የቤት አሰራሮች ውስጥ አንዱን በቀለም ሰርታችሁ አሳዩ፡፡ የሰራችሁትን ስዕል አሰራሩን ግለፁ፡፡

## ማጠቃለያ

ከላይ እንደተቀመጠው የሙዚቃን ጠቀሜታ በተለያየ መንገድ ተረድታችኋል፡፡ ሙዚቃ ድምፆችን ከመስማት ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ስላለው ከላይ የተጠቀሱትን ቅኝቶችንና የተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ሰምቶ ለመለየት ሙዚቃን ደጋግሞ በጥልቀት መስማት አስፈላጊ ነው፡፡

የዕይታ ጥበባት አካባቢን በጥልቀት ማስተዋልን እንዲሁም በማስተዋል ማሰብን ይጠይቃሉ፡፡ የዕይታ ጥበባት ከስነ-ዉበት አስተሳሰብ እና ትርጉም ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው፡፡ የዕይታ ጥበባትን መስራት ለአዕምሮ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው፡፡ የዕይታ ጥበባት ለማህበረሰባዊ እድገት ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡ የዕይታ ጥበባትን ለማድነቅ የዕይታ ጥበባቱ በማህበረሰቡ ታሪክ ውስጥ ያላቸውን ጠቀሜታ ማወቅ ተገቢ ነው፡፡ በሀገራችን ብዙ ዓይነት የቤት አሰራር አይነቶች ይገኛሉ፡፡ በሀገራችን የሚገኙ የቤት አሰራሮች አካባቢያቸውን መሰረት አድርገው የሚሰሩ ናቸው፡፡

## የማጠቃለያ ምዘና

፩. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ፡፡

1.ሙዚቃን መለማመድ ለምን ለምን ይጠቅማል፡፡

2.ባህላዊ ሙዚቃ የሚያስብለው ምክንያት ምንድን ነው

3.ስለ ክራር የምታውቁትን ግለፁ

4. የዕይታ ጥበባትን መስራት ያለውን ጠቀሜታ በአጭሩ ፃፉ፡፡

5. የዕይታ ጥበባትን መለማመድ (መስራት) ያለውን ጠቀሜታ በስንት ዋናዋና ክፍሎች ከፍለን እናያለን? ምን ምን ናቸው?

6. የዕይታ ጥበባትን መስራት ለማህበረሰባዊ ግንኙነት ያለውን ጠቀሜታ ፃፉ፡፡

7. የሀገራችንን የቤት አሰራሮች ከምን ከምን አንፃር እንደሚሰሩ ግለፁ፡፡

## 5.1 ሙዚቃን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማዛመድ፡፡

ሙዚቃን በመማር ማስተማር ሂደቱ እንደ አንድ የማስተማሪያ ዘዴ መጠቀም ውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲኖር ከማድረጉም በላይ ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት አይነት የሚጠበቀውን ውጤት እንዲያመጡ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ ሙዚቃን ከተለያዩ የትምህርት አይነቶች ጋር በቀላሉ ማዛመድ ይቻላል ለምሳሌ የሂሳብ ትምህርትን ዜማ እና ግጥምን ተጠቅመን የመማር ማስተማሩን ሂደት ማከናወን ተማሪዎች አእምሮአቸው ሳይጨነቅ እና አሰልቺ ባልሆነ መንገድ በቀላሉ የሂሳብ ስሌቶችን እንዲረዱ ማድረግ ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ቋንቋን፣ሳይንስን፣ሂሳብን፣ ታሪክን እና ባህልን ለማስተማር ሙዚቃን እንደ አንድ የማስተማሪ ስልት መጠቀም ውጤታማ የሆነ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲኖር ያደርጋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከአንድ የትምህርት ክንውን ወደ ሚቀጥለው ክንውን ለመሸጋገር ሙዚቃን መጠቀም የተማሪዎችን ስሜት በተነቃቃ ሁኔታ ለሚቀጥለው ትምህርት ዝግጁ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

**የትምህርቱ ዝርዝር አላማ፡-**

- ተማሪዎች በቡድን ትዘምራላችሁ
- ቤተሰባዊ ድርጊቶችን የተመለከቱ መዝሙሮችን ትዘምራለችሁ
- ስለ ተፈጥሮ ትዘምራላችሁ

## 5.1.1 ሙዚቃን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማዛመድ፡፡




**መዝሙር 1፡- ተፈጥሮን መንከባከብ**

የመዝሙር 1፡- ተፈጥሮን መንከባከብ

1. አረንጓዴ ተክሎችን
እንከባከባቸው፣
አበባን መቅጠፍ፣
ወንዞችን መበከል፣
ዛፎችን መቁረጥ
በጣም አደገኛ ነው፡፡

2. የተፈጥሮ ሀብቶችን ፣
መጠበቅ ይገባል፣
ውሀን ማባከን
ተፈጥሮ ያዛባል፣
ዛፎችን መቁረጥ
መሬት ይሸረሽራል፡፡

መልመጃ 1፡-

1. ከላይ ተቀመጠውን መዝሙር መልዕክት ባጭሩ ለመምህራችሁ ግለፁ
2. መዝሙሩን በግል ተለማምዳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ
3. የመዝሙሩን መልዕክት ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት

መዝሙር 2፡-የስነ ምግባር መዝሙር

የመዝሙር 2 ፡- የስነ ምግባር መዝሙር

እኔ ሀገሬን እወዳለሁ

እናት እና አባቴን

አከብራቸዋለሁ

ለታናሽ ለታላቁም

እታዘዛለሁ

ሰዎችን ለመርዳት

እችኩላለሁ

አዎ

መልካምነትን አሳያለሁ፡፡

መልመጃ 2፡-

1. ከላይ ተቀመጠውን መዝሙር መልዕክት ባጭሩ ለመምህራችሁ ግለፁ
2. መዝሙሩን በግል ተለማምዳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ
3. የመዝሙሩን መልዕክት ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት

## መዝሙር 3፡-




ትምህርት ይጣፍጣል (የቀድሞ
የትምህርት ቤት ዜማ)

ትምህርት ይጣፍጣል ከማር ከወተት

ከማር ከወተት

ያርማል ስህተት፡፡

ውቢቷ ሀገራችን ለምለም እናታችን

ትመግበናለች እንደማር ወተት፡፡

## መልመጃ 3፡-

1. ከላይ ተቀመጠውን መዝሙር መልዕክት ባጭሩ ለመምህራችሁ ግለፁ
2. መዝሙሩን በግል ተለማምዳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ
3. የመዝሙሩን መልዕክት ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት

መልመጃ 4

ሆሄያቱን ከኖታው ትክክለኛ የጊዜ ቆይታ ጋር በትክክለኛው ድምፅ ለመዘመር ተለማመዱ፡፡

ከላይ የተቀመጡትን የመዝሙር ግጥሞች በቃላችሁ አጥኑ፡፡

1. ከላይ የተቀመጡትን መዝሙሮች መልዕክት ባጭሩ ለመምህራቸው ይግለፁ፡፡

2. መዝሙሩን በግል ተለማምደው ለክፍል ጓደኞቻቸውሲያቅርቡ አቀራረባቸውን ይመዝኗቸው፡፡

5.2 የውዝዋዜና ትያትር ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማዛመድ፡

የውዝዋዜ ድርጊቶች በተለያየ መንገድ ከተፈጥሮ እና ከእንስሳት ይከተባሉ፡፡ ይህም ከሳይንስ ትምህርት ጋር በእጅጉ የሚዛመድ ነው፡፡ ተማሪዎች የአጸዋትን እንቅስቃሴ ለውዝዋዜ በምታጠኑበት ወቅት ስለ እጸዋት ስነ-ተፈጥሮ እግረመንገዳችሁን ታውቃላችሁ ማለት ነው፡፡ ስለ እንስሳት እንቅስቃሴ ለማጥናት በምታደርጉት ሂደት ከውዝወዋዜው ድርጊት ባለፈ ስለ እንሰሳት ስነ-ባህሪ ታውቃላችሁ ማለት ነው፡፡ ይህም ከሳይንስ ትምህርት ጋር የተቆራኘ ያደርገዋል ማለት ነው፡፡

ዝርዝር አጥጋቢ የመማር ውጤት

- በሚና ጨዋታ ከእፀዋት ውዝዋዜን ትቀዳላችሁ
- የእንስሳትን እንቅስቃሴ በውዝዋዜ ታስመስላላችሁ
- የተለያዩ አይነት የእንቅስቃሴ ምንጮችን ታውቃላችሁ

### 5.2.1 ከዕፀዋትና ከእንሰሳት እንቅስቃሴዎችና ውዝዋዜዎችን መቅዳት

ከዚህ በፊት በነበሩት ምዕራፎች ስለ ውዝዋዜ ምንነት ተምራችኃል። ውዝዋዜ በተለያየ የመልከአ ምድራዊ ክልል በተለያየ ባህል የሚገኙ ህዝቦች የሚያውቁት፣የሚገለገሉበትና ለተለየ አላማቸው ሲሉ በወጉ የሚከሽኑት ጥበብ ነው። ይህንንም እንቅስቃሴ ማህበረሰቡ በአደን፣ በሰርግ፣ በልዩ ልዩ ባህላዊና ሀይማኖታዊ በዓላት፣ በእርሻና በመሳሰሉት ጉዳዮች ሲጠቀምበት ቆይቷዋል። እነዚህ የውዝዋዜ ድርጊቶች በተለያየ መንገድ ከተፈጥሮ እና ከእንስሳት እንቅስቃሴ ይከተባሉ።


**5.2.2 ውዝዋዜ:-** ልዩ ልዩ ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴዎችን በመቅዳት ይታወቃል፡ ፡ ከነዚህም እንቅስቃሴዎች መካከል ዛፍ ንፋስ በሚያወዛውዘው ጊዜ ያለውን እንቅስቃሴ በመከተብ፤ እሳት ሲነድ፣ የጦጣ፣ የድመት፣ እባብ ለመናደፍ ሲል፣ ውሻ አሳዳጊውን ሲያይ እና ሌሎችም እንቅስቃሴዎችን በመቅዳት ለዳንስ ግብዓትነት ሲጠቀሙበት እንመለከታለን። በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ዳንስ ውስጣዊ ስሜትን፥ ፍቅርን፥ ንዴትን፥ ቅናትን፥ ጀግንነትን፥ ሀዘንንና የአካባቢ ውበትን በማድነቅ ከቃላትና ከቁሳቁስ ቀድሞ የነበረ በጠቅላላ አካላት አማካኝነት የሚገለፅ የእንቅስቃሴ ቋንቋ ነው።

በድሮ ጊዜ አባቶቻችን ለአደን በሚወጡበት ጊዜ እንሰሳትን ለማደን ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎችን ያደርጉ ነበር።










ስዕል 2 በአደን ወቅት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች

- ተማሪዎች ከዚህ በመቀጠል የተለያዩ ተፈጥሮአዊ እና የእንስሳት እንቅስቃሴዎችን በመከተብ በውዝዋዜ አቀናጅታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ስዕል 3 ዛፍ በንፋስ ሲወዛወዝ የሚያሳየው እንቅስቃሴ




ስዕል 4 እባብ ለመናደፍ የሚያደርገው እንቅስቃሴ



ስዕል 5፡- ውሻ አሳዳጊውን ሲያይ የሚያደርገው እንቅስቃሴ




ስዕል 6፡- ድመት ስትጫወት የምታሳየው እንቅስቃሴ



ስዕል7፦ እሳት ሲነድ የሚታየው እንቅስቃሴ



ስዕል 8፦ የጦጣ የምታሳየው ልዩ ልዩ እንቅስቃሴ



መልመጃ1፦ ከዚህ በላይ የተመለከታችሁትን ምስሎች መሰረት በማድረግ በቡድን በመሆን የእንስሳቱን እንቅስቃሴ በውዝዋዜ አሳዩ፡፡

## 5.4 የዕይታ ጥበብን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማዛመድ

ቀደም ባሉት ምዕራፎች ስለ ፎርም ቅርጽ እና ቀለም ተምረናል እንዲሁም የዕይታ ጥበባትንመለማመድ ያለውን ጠቀሜታ አይተናል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ የዕይታ ጥበባትን እና የተለያዩ የትምህርት አይነቶችን አጣምሮ መማር ያለውን ጠቀሜታ እናያለን በተጨማሪም ሌሎች የትምህርት አይነቶች ላይ እንዴት መጠቀም እንደምንችል እናያለን፡፡

### 5.4.1 ቅርፆችን፣ ፍርሞችንና ቀለማትን ከሒሳብ የትምህርት ዓይነትና ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማዛመድ

**የትምህርቱ ዝርዝር አላማ፡-**

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራቹ በኋላ


- የዕይታ ጥበባትን ከሌሎች ትምህርቶች ጋርአቀናጅቶ መማር ያለውን ጠቀሜታ ታውቃላቹ
- የዕይታ ጥበባት ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶት ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ታውቃላቹ
- ስዕላዊ ቅርፆች ከሒሳብ እና ሳይንስ ትምህርቶች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ታውቃላቹ
- ቀለማት ከሳይንስ ጋር ያላቸውን ዝምድና ታያላቹ

### 5.4.2 የዕይታ ጥበብና የሒሳብ ትምህርት ጥምርታ


በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴያችን እንዲሁም በኑሯችን የምንመለከታቸው ቁሶች በሒሳብ ትምህርት ውስጥ ከምናገኛቸው የተለያዩ ጂኦሜትርያዊ ቅርፆች ጋር የሚያያዙ ናቸው:: እነዚህን ቅርፆች ጂኦሜትሪያዊ እና ተፈጥሯዊ በማለት በ ሁለት እንከፍላቸዋለን:: ጂኦሜትሪያዊ የምንላቸው የራሳቸው ወሰናዊ መስመር፣ ጠርዝ እንዲሁም ወለል ያላቸው ባለ ሁለት አውታረ መጠን የሆኑ የተለያዩ ቅርፆች ናቸው:: እነዚህ ቅርጾች እንደ ክብ፣ አራት ማዕዘን ፣ ሶስት ማዕዘን የመሳሰሉት ናቸው:: ከቅርፆች በተጨማሪ ቀለማትን በሂሳብ ትምህርት ውስጥ በስፋት ልናገኛቸው እንችላለን በተለይም እያንዳንዳቸው ቀለማት ያላቸውን የመታየት አቅም ለማወቅ እንዲሁም ለመገልፅ ሂሳባዊ ቀመሮችን እንጠቀማለን ይህም የተለያዩ ቀለማትን ለመለየት እና የትኛው ከየትኛው የበለጠ ይታያል የሚለውን ለማውቅ በምናደርገው ሒሳባዊ ስሌት አማካኝነት የቀለማትን ባህሪ እያወቅን ሒሳባዊ ችሎታችንንም እናሳድጋለን::

### 5.4.3 የቅርፆች ዓይነት


ቅርፆች የሚገልፁት (የሚወክሉት) የራሳቸው የሆነ ባህሪያት አሏቸው። እነዚህ ባህሪያት የሚወሰኑት በዓይናችን ካየናቸው በኋላ በሚፈጥሩብን ስሜት ነው።



**5.4.4 ሶስት ማዕዘን፦** ሶስት ማዕዘን ባለ ሶስት ጎን ቅርፅ ሲሆን በስዕል ስራ ውስጥ ሶስት ማዕዘን ጠንካራ የሆነ ቅርፅ (የጥንካሬ) መገለጫ ነው።



**5.4.5 ክብ፦** ክብ የምንለው ከሁሉም አቅጣጫ እኩል በሆነ ነጥብ ዙሪያ የተሰመረ መስመር ነው። ክብ ቅርፅ በስዕል ቋንቋ ውስጥ የሴቴ ባህሪን የሚያመለክት ቅርፅ ነው።



**5.4.6 ካሬ፦** በአራቱም ማዕዘን እኩል የሆነ ቅርፅ ሲሆን በስዕል ውስጥ ክብደትን ለማሳየት እንጠቀምበታለን።

### 5.4.7 የዕይታ ጥበብና የሳይንስ ትምህርት ጥምርታ


ሳይንስ ምልከታን እና የተለያዩ ጥያቄዎችን መመለስ ላይ እና የተለያዩ ምርምሮችን በማድረግ ላይ መሰረት ያረገ ትምህርት ነው። የዕይታ ጥበባት ደግሞ ሀሳብን፣ ምልከታን፣ ውበትን የመሳሰሉት ነገሮች ላይ ትኩረት በማድረግ የሚሰሩ ናቸው። የሳይንስ እና ስነ-ጥበብ የመጨረሻ ግባቸው የተለያየ ቢሆንም እንኳ የሚሰሩበት እና የሚተገበሩበት መንገድ ተመሳሳይ ነው።


የዕይታ ጥበብን ለመስራት አካባቢያችንን በምናስተውልበት ወቅት የተለያዩ ሳይንሳዊ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ሳይንሳዊ ዕውቀታችንን እናሳድጋለን። እንዲሁም የምናባዊ ፈጠራ ችሎታችንን ስለምናሳድግ በሳይንስ ላይ በዐይን የማይታዩ

ነገሮችን በምንማርበት ወቅት የራሳችንን ምስል እንድፈጥር እና የምንማረውን ትምህርት ልዩ በሆነ መንገድ መረዳት እንችላለን። ይህም ለትምህርቱ ያለንን ፍቅር እንድናዳብር እና ትምህርቱም ቀላል እና አዝናኝ እንዲሆን ይረዳናል።

ቀለማት የስነ ጥበብ መሰረታውያን ሲሆኑ ከሳይንስ አንፃር ስንመለከታቸው ደግሞ የራሳቸው ልኬት ያላቸው ናቸው። እንዲሁም እርስበርስ ሲቀላቀሉ አዲስ አይነት ቀለምን ይሰጡናል። ይህም በሳይንስ ትምህርት ውስጥ ውህድ ተብሎ ይጠራል። ስለዚህ ቀለማትን በመጠቀም የተለያዩ ሳይንሳዊ ሙከራዎችን ማድረግ እንችላለን። ሌላው ከቀለም ጋር የሚያያዘው ሳይንሳዊ ሙከራ የሊትመስ ወረቀትን በመጠቀም አሲድ እና ቤዝን በወረቀቱ ቀለም መለወጥ ልንለያቸው እንችላለን።

### 5.4.8 የቀለማት መዋሀድ





## ማጠቃለያ

ሌሎች እውቀቶችን በሙዚቃ ማስተላለፍና እንዳይረሳ ለማድረግ የተሻለ መንገድ መሆኑን ከላይ ባየናቸው ምሳሌ መዝሙሮች መገንዘብ ይቻላል። ሌሎችንም ትምህርቶች በሙዚቃ በማቅረብ ጥሩ ውጤት ለማስመዝገብ ሞክሩ።

በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴያችን እንዲሁም በኑሯችን የምንመለከታቸው ቁሶች በሒሳብ ትምህርት ውስጥ ከምናገኛቸው የተለያዩ ጂኦሜትርያዊ ቅርፆች ጋር የሚያያዙ ናቸው። ቀለማትን በሂሳብ እና በሳይንስ ትምህርት ውስጥ በስፋት ልናገኛቸው እንችላለን። ቀለማት ያላቸውን የመታየት አቅም ለማወቅ እንዲሁም ለመገልፅ ሂሳባዊ ቀመሮችን እንጠቀማን። ቅርፆች የሚገልፁት (የሚወክሉት) የራሳቸው የሆነ ባህሪያት አላቸው። የሳይንስ እና ስነ-ጥበብ የመጨረሻ ግባቸው የተለያየ ቢሆንም እንኳ የሚሰሩበት እና የሚተገበሩበት መንገድ ተመሳሳይ ነው። የዕይታ ጥበባት ለሳይንስ ትምህርት ያለንን ፍቅር እንድናዳብር እና ትምህርቱም ቀላል እና አዝናኝ እንዲሆን ይረዳናል። ቀለማት የስነ ጥበብ መሰረታውያን ሲሆኑ ከሳይንስ አንፃር ስንመለከታቸው ደግሞ ልኬት ያላቸው ናቸው።

## የማጠቃለያ ምዘና

፩ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዶ ቦታውን በትክክለኛው አረፍተ ነገር ሙሉ።

1. አረንጓዴ ተክሎችን ................
2. አበቦች ................፣ወንዞችን ................፣ዛፎችን......... በጣም አደገኛ ነው።
3. ውሀን ማባከን ተፈጥሮን ያዛባል ዛፎችን መቁረጥ ..............
4. ተፈጥሮን መንከባከብ በሚለው መዝሙር ውስጥ ስንት ሩብ ኖታ እናገናለን..............
5. የስነ ምግባር በሚለው በሚለው መዝሙር ውስጥ ስንት ግማሽ ኖታ አለ............

6. ትምህርት ይጣፍጣል ከማር ከወተት ከማር ከወተት...........
7. ትምህርት ይጣፍጣል ከሚለው መዝሙር ውስት ስንት የሩብ ኖታ እረፍት ምልክት አለ.............
8. ውቢቷ ሀገራችን ለምለም እናታችን ትመግበናለች ................

፪ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ ፃፉ::

___________1. በስዕል ስራ ውስጥ ጠንካራ የሚባለው ቅርፅ የትኛው ነው::

ሀ. አራት ማዕዘን ለ. ሦስት ማዕዘን ሐ. ካሬ

መ. ሁሉም

___________2. የራሳቸው ወሰናዊ መስመር፣ ጠርዝ እንዲሁም ወለል ያላቸው ባለ ሁለት አውታረ መጠን ያላቸው ነገሮች___________ በመባል ይታወቃሉ::

ሀ. ቀለማት ለ. ቅርጾች ሐ. መስመሮች

መ. ሀ እና ሐ

___________3. ከሚከተሉት ውስጥ እርስበእርሳቸው የሚቀላቀሉት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. መስመሮች ለ. ሦስት ማዕዘን ሐ. ቀለማት

መ. አራት ማዕዘን

___________4. ከሚከተሉት ውስጥ የተለየ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. አራት ማዕዘን ለ. ካሬ ሐ. ኮን

መ. ሰማያዊ

___________5. ከሚከተሉት ውስጥ የስነ ጥበብ መሰረታውያን የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ቅርፅ ለ. ቀለም ሐ. ፎርም

መ. ሁሉም

# ዋቢ መፃህፍት

1. ታሪክና ምሳሌ፣ ክቡር ደ/ር ከበደ ሚካኤል (1999)
2. ባህሩ ዘወዴ (1999) የኢትዮጵያ ታሪክ 1847-1983፤
3. Ezra Abate, (2009) Ethiopian kinit (scales), Analysis of the formation and structure of the Ethiopian scale system
4. Ashenafi kebede, (1971) The music of Ethiopia ;its development and cultural setting
5. Ellinger, J. (2014) Music theory fundamentals
6. Jones, Russel and Cathrine ( 2021) , understanding basic music theory
7. Bahru Zwede ,(2002) The history of modern Ethiopia 1855- 1991
8. የኢትዮጵያ ሙዚቃ ታሪክ 1889-1983 ተስፋዬ ለማ (2005)
9. The little book of music theory, Amsco Publications, New York.
10. Harmony 1, Barrie Nettles, Berklee collage of music, (1987)

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

2014 ዓ.ም / 2021 /